# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አሻራ በሸካቾ ብሔር

ወንድምስሻ አየለ አንገሎ*

## Abstract:

Anyone looking at the ethnic identity, culture and language of the ‘Shekacho’ nation, who inhabit the Sheka Zone of the Southern Nations Nationalities and People’s Regional State of Ethiopia, discovers traces of the heritage of the EOTC. Looking at this heritage in the light of the contemporary teaching of the EOTC, we are able to gain remarkable insights concerning religious values, and matters of government interest. This research is devoted to identifying the footprints of the Church in the Nation, complemented by other research it constitutes a benchmark for viewing the Church’s history upstream of the Gibie River.

The research was centered on the Andiracha district of Sheka Zone, which is justified by the fact that it was the last seat of the Shekacho Dynasty, where the society assembled and their important fortification was located. In the course of this research efforts are made to analyze the data from interviews with elders of the nation, supplemented by previous research by scholars and a team of professionals organized by the zonal administration, with the addition of information from various books. The outstanding footprints of the Church are seen in ceremonies, folklore concerning the observance of Lent, the mode of worship on Good Friday including the special type of singing, the festivities of festivals of the angels, Saints, Virgin Mary, that includes places and groups in the commemoration of the names of the Saints, the terminology and specific names used in the local calendar, including the presence of thirteen months etc.. All these justify the assumption of a strong foundation of EOTC influence previously. Finally, it is recommended that the scholars priests and administration of the Church should devote more time and effort to strategically reviewing the planning and carrying out of public services and communications in the area upstream of Gibei. The complex ideologies of different groups which are propagated as if the Church were absent from the area, would be challenged and refuted publically, while at the same time contributing to the energetic maintenance of the outstanding values of the Church and nation.

* ወንድምስሻ አየለ አንገሎ የሲቪል ምህንድስና ባለሙያ እና የብሔረሰቡ አባል ነው፡፡

## ፩. መግቢያ

ክቡር ፍጡር የሆነው ሰውና የልዑል ፈጣሪ ረቂቅ ግንኙነት የሚደረግበት ሃይማኖት በባህል፣ በቋንቋና በታሪክ ላይ የራሱ ድርሻ ይኖረዋል፡፡ ታሪክ፣ ባህልና ቋንቋም የየዕለት ሕይወት የሚገለጽባቸው፣ የአንድ ሰው ብሎም የብሔረሰቦች[1] ሃይማኖታዊ ሕይወት አሻራ የሚያርፍባቸው ናቸው፡፡ በዚህ መሠረት የሸካ ብሔረሰብእ አባላት ነባርና እንደ ብሔረሰብእ ወጥነት የሚታይበት፣እንዲሁም በባህሉና በቋንቋው የሚገልጸው ሃይማኖት ሊኖረው እንደሚችል ብዙ ማተት አያስፈልግም፡፡

በዚኽ ጥናት የሸካ ብሔረሰብእ በባህሉ፣ በታሪኩና በቋንቋው ውስጥ ለረዥም ዘመናት ያቆየውን ሃይማኖታዊ አሻራ መፈለግና ከኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ትምህርትና ሥርዐት ጋር በማገናዘብ የብሔረሰቡኡን ኦርቶዶክሳዊ ገጽታ ለመለየት ተሞክሯል፡፡ ጥናቱ ለሌሎች ብሔረሰቦች ተመሳሳይ ጉዳዮችም ማነጻጸሪያ ይሆናል፡፡ የብሔሩን ታሪክ በአጭሩ ማየት የጥናቱን ይዘት ለመረዳት ስለ ሚጠቅም በአጭሩ በዚህ ክፍል እናየዋለን፡፡

የሸካቾ ብሔረሰብእ በደቡብ ኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በዋናነት በሸካ ዞን፣ በተጨማሪም በጋምቤላና ኦሮሚያ ክልሎች የሸካ ዞን አዋሳኝ ወረዳዎች ውስጥ የሚገኝ ብሔረሰብእ ነው፡፡ የሸክኛ ቋንቋም (ሸኪኖኖ) በኦሞቲክ የቋንቋ ቤተሰብእ ይመደባል፡፡ በ፲፱፻፺፱/፳፻ ዐ.ም. በመንግሥት በተደረገው ሀገር ዐቀፍ የሕዝብና ቤት ቈጠራ ውጤት መሠረት በመላው ኢትዮጵያ የሸካቾ ብሔረሰብእ አባላት ቍጥር ፯፻፴፯፻፴፰ ነው፡፡ በብሔረሰቡ ውስጥ እስከ ፲፱፻፹፯ ዐ.ም. ድረስ እስልምናን የተቀበለ አንድም ሸካቾ አልነበረም፡፡ ከ፲፱፻፶ዎቹ መጀመሪያ ጀምሮ ደግሞ የፕሮቴስታንት እምነት ድርጅቶች ገብተው እየተስፋፉ ይገኛሉ፡፡

ከብሔረሰቡ የታሪክ ምንጮች[2] ያገኘነው መረጃ ሕዝቡ ከእስራኤል እንደ መጣ ያስረዳል፡፡ አውግቸው ወርቅ አገኘሁ (፲፱፻፹፯) ‹‹ብሔረሰቡ የመጣው ከኤስያ፣ ‹‹አሾአምበላ›› ከሚባለው ቦታ እንደሆነ ፣ ኦሾ ማለት ኤስያ ነው፤ ምናልባትም ከእስራኤል ልዩ ስሙም ‹‹ኡምብሪካሽ››[3] እንደሆነ ነው የሚናገረው›› ብለዋል፡፡[4] ዋርነር ጄ. ላንጌ በበኩላቸው ‹‹አባቶቻችን እንደነገሩን የመጣነው ከእስራኤል ነው፤ የሞቻ ሕዝብ እስራኤልን ትቶ ወደ አኩሱም ፈለሰ፤ ከአኩሱምም በሂናርያ አሁን ካሉበት ደረሱ፡፡ እነርሱም ፲፪ ታቦታት ከእስራኤል ይዘው መጥተዋል፡፡ ታቦታቱም ከአብርሃም ልጅ ነው የተሰጣቸው፡፡››[5] ብለዋል፡፡

[1] ብሔር፣ ብሔረሰብእ እና ሕዝብ የሚባሉትን ስያሜዎች በየመነሻ ጽንሰ ሐሳባቸው ስለሚለያዩና በተወሰነ መልክም ፖለቲካዊ አንድምታ ስላላቸው በዚኽ ጥናት ውስጥ በተለዋዋጭነት እንጂ በተለየ ትርጉም መጠቀም አልተፈለገም፡፡

[2] የታሪክ ምንጮች የምንላቸው የብሔሩ ታሪክ ዐዋቂ ሽማግሌዎች ያቀረቡት አፈ ታሪክ፣ በየክፍሉ የሚጠቀሱት ያልታተሙ ጽሑፎችና ጥቂት የታተሙ መጻሕፍት ናቸው፡፡ የእነዚህ የታሪክ ምንጮች ተገቢነት በጥናቱ አዘጋገብ ርእስ ሥር ተብራርቷል፡፡

[3] ስለ ሕዝቡ ወደ ኢትዮጵያ አገባብ ሰፊ ጥናት መፈለጉ አይቀርም፡፡ የጎንጋ/ግቤ መንግሥታት አመጣጣቸው ከሰሜን መሆኑ ብዙም አያጠያይቅም፡፡ ነገር ግን የመነሻቸውን ቦታና ዘመን ለመለየት የሚያስችል ጥናት መደረግ አለበት፡፡ በግእዝ ብቻ የሚገኘው ታሪከ ነገሥት ላይ የቀዳማዊ ምኒልክን ግዛቶች ሲጠቅስ ‹‹ነገደ አብሂም›› የተባለው ማኅበረሰብእ ‹‹ወትእይንቱ ካፋ›› በማለት የአካባቢው አስተዳደር ማእከል (መናገሻ) ካፋ እንደሆነ ይናገራል፡፡ አካባቢው ከማእከላዊ መንግሥት ጋር ያለውን ሃይማኖታዊ ግንኙነት የሚያጠናክረው ደግሞ በዚሁ በታሪከ ነገሥት ውስጥ በተለይ ከዐራቱ የጎንጋ ሕዝቦች አንዱ የእናርያ ሕዝብ በስፋት መጠቀሱ ሲሆን፣ በዘመነ ዛጕዌ ዮሴፍ ዘእናርያ የተባሉ የአቡነ ኢየሱስ ሞዐ ደቀ መዝሙር በመምህርነት እንደተላኩለት፣ በጎንደሩ አድያም ሰገድ ኢያሱም ከሰሜን ሸዋው ደብረ ሊባኖስ ገዳም በተሻለ ሁኔታ ከግራኝ ዘመን ጥቃት የተረፉ አብያተ ክርስቲያናት በእናርያ እንደነበሩ በጉብኝታቸው ማየታቸውን በየነገሥታቱ ታሪክ ክፍል ተጠቅሷል፡፡ (ታሪከ ነገሥት፤ ግእዝ፤ ያልታተመ፤ በየነገሥታቱ ታሪክ ክፍል) ከዚህ የሚለየውና በጥልቅ መጠናት ያለበት ጉዳይ ደግሞ በሸካ ታሪክ እና በአሁኗ ማእከላዊ ኢጣሊያ አካባቢ ነበሩ ስለሚባሉ የኡምብሪ ማኅበረሰብእ የዘመን፣ የስያሜዎችና የፍልሰት ሁኔታዎች ተቀራራቢነት ነው፡፡ በሸካቾ የዘር ሐረግ ውስጥ ‹‹በራዶ›› የተባለው የጎሳዎች ግንድ ትርጕሙ ‹‹ሌላ ዘር›› የሚል መሆኑም ለታሪኩ ጥናት አስፈላጊ ሐቅ ነው፡፡ (Guy Jolyon Bradley, *Ancient Umbria: State, Culture, and Identity in Central Italy from the Iron Age to the Augustan*, (Oxford University Press Incorporated, 2000). Collins English Dictionary – Complete and Unabridged, (Harper Collins Publishers, 2003).

[4] አውግቸው ወርቅ አገኘሁ፤ ‹‹ትውፊትና ባህላዊ ክንዋኔ በሸካ ብሔር›› (፲፱፻፹፯፤፱) (ያልታተመ)፡፡

[5] Warner J. Lange, The *History of Southern Gonga*; p. 123. ይኽን ታሪክ ጸሓፊው በተረዱት (በተነገራቸው) መልክ ዘግበውት እንደሁ እንጂ ታቦትና የአብርሃምን ልጅ እንዲኹም የታቦቱ ብዛት ፲፪ መኾንና የኦሪታዊው ዘመን የታቦት ታሪክ አይስማሙም፡፡ ምክንያቱም ታቦት የተሰጠው የአብርሃም የልጅ ልጅ ያዕቆብ ከልጆቹ ጋር ግብጽ ከተሰደደና በግብጽ በባርነት ከወጡ በኋላ በሲና በረሀ በመሆኑ ቢያንስ የ፭፻ ዐመታት የዘመን ልዩነት ስላለው፤ በኦሪት የነበረው ታቦትም ኹለት ብቻ ስለነበረ ነው፡፡ (የሐዋ. ፯፥፪-፴፰)

የሕዝቡ ባህል በመጽሐፍ ቅዱስ ለአይሁድ የታዘዘውን *መሥራታቸውን* ከእስራኤል ለመምጣታቸው አስረጅ አድርገው የብሔረሰቡ ሽማግሌዎች[6] ይናገራሉ፡፡ ለምሳሌ ሰው የሞተበትን ቤት ማፍረስ፣ ሴት በወር አበባ ጊዜዋ ርኩስ ተብላ መገለል፣ በተራራ ላይ መሰዋት፣ የመገረዝ ባህል፣ የሟች ሚስት ለወንድም ማጋባት እና ሌሎችም ወደ ፊት ይጠቀሳሉ፡፡[7] እነዚኽንም በዝርዝር እናያቸዋለን፡፡ እስከ ኢትዮጵያ ምድር ያለውን የጉዞ ሁኔታ እና ዘመን የሚያስረዳ ከአፈ ታሪክ ያለፈ አሳማኝ ማስረጃ ባይገኝም ወደ ኢትዮጵያ ምድር (አኩስም) ከገቡ በኋላ ለኹለት ተከፍለው በወሎ በኩልና በጎጃም በኩል ወደ በዲኢላ (በደሌ) እንደተጓዙ፣ ኹለት ወንድማማቾችም[8] መንገድ እንደቀሩ ሽማግሌዎች ያስረዳሉ፡፡ በጉዞአቸው በወሎ፣ ማሻና ሺበሆ እንዲሁም በወለጋ አንፊሎ የቋንቋና ስያሜ ዝምድና ሕዝቡ የተወሰነ ጊዜ ሠፍሮባቸው ወይም ከሕዝቡ ተከፍለው ተቀምጠውባቸው እንደኾነ ይነገራል፡፡

ከአንድ *ሥፍራ* በአንድ ላይ የተነሡት በታሪክ መጻሕፍት እናርያ የሚባለውና አሁን ተለይቶ የሚኖርበት ቦታና ማንነቱ የማይታወቀው (በሸክኛ ሂናሮ የሚባለው)፣ አሁን በካፋ ዞን የተከለለው ካፋቾ፤ ቦሾ (አሁን የት እንዳለ አይታወቅም) ከሸካቾው ሕዝብ ጋር አብረው ተጓዙ፡፡ ቀድሞ የደረሰው ሂናሮ ኦጋሮ አካባቢ ሠፍሮ ቆይቶ ሸካቾው ሲደርስ እንዲገብርለት ሲጠይቀው ሸካቾው ‹‹የአንድ ነገድ የሴም ልጆች ሆነን አልገብርልህም›› በማለት በመቃወሙ ወደ ጦርነት አምርተዋል፡፡ ከዐሥራ አምስት ዐመት ጦርነት በኋላ (አንድ ዐመት የሚሉ አሉ) በሽማግሌ ታርቀው ከበዲኢላ (በደሌ) ጀምሮ ወደ ምዕራብ ያለው ለሸካቾ፣ ኦጋሮ፣ ሊሙ ጅማን ጨምሮ ለሂናሮ ተከልሎላቸው ሳይገባበሩ ኖረዋል፡፡ ከዚህ በኋላ ተረጋግተው ንጉሥ ሾመው በደሌን መናገሻ አድርገው ሲኖሩ በስምንተኛው ንጉሥ በዲጋዎች[9] ዘመን ከኦሮሞ ሕዝብ ጋር በተደረገ ጦርነት ‹‹አልገብርም፣ ቦታ አልሰጥም›› ያለው ከንጉሡ ጋር ወደ ሰሌ ኖኖ (አሁን በኦሮሚያ ክልል ኢሉ አባቦራ ዞን ውስጥ ያለ ወረዳ) እንደመጣ የቀረውም ኦሮሞን መስሎ ገብሮ እንደኖረ፣ የአሁኑ በደሌ ወረዳ ገቺ አካባቢ የነገሥታትና የጦር መሪዎች፤ የጦር ማሠልጠኛ የነበሩ ቦታዎች አሁን ጭምር ተለይተው እንደሚታወቁ ሽማግሌዎቹ ያስረዳሉ፡፡

ከኦሮሞ ሕዝብ ጋር ከመዋጋቱ በፊት የግራኝ አሕመድ ወረራ እንዳጋጠማቸው በስፋት ከመተረኩ በተጨማሪ በውጪ ሀገር ጸሐፍትም ተመዝግቧል፡፡[10] የግራኝ አሕመድን ወረራ[11] ፈርተው በሀገሩ ሰላም ነግሦ አምልኳቸውን በተሟላ መልክ እስኪፈጽሙ ድረስ አኢአች ወደተሰኘው ወንዝ ሄደው በውኀው ተጉመጥምጠው እንዲህ ብለው ለወንዙ አደራ ሰጡ፤ ‹‹አንተ ወንዝ የክርስትና እምነታችንን ተቀብለህ አደራ አስቀምጥ፣ አንድ ቀን መልሰን እንወስዳለን፡፡›› ይህን ብለው ከወንዝ የተጉመጠመጡትን ውኀ ወንዙ ውስጥ በመትፋት አደራቸውን ሰጡ፡፡

---

[6]የብሔረሰቡ ሽማግሌዎች እያልን በዚኽ ጥናት ውስጥ የምንጠራቸው በዕድሜም ሆነ በብሔረሰቡ ዘንድ ባላቸው ተቀባይነት የብሔረሰቡን ታሪክና ባህል ሊያስረዱን ይችላሉ ብለን በዋናነት ከአንድራቻ ወረዳ የመረጥናቸውና በጥናቱ አዘጋገብ ርእስ ሥር የዘረዘርናቸው ዐረጋውያን ናቸው፡፡

[7] ዘሌ. ፲፬ ፥ ፲፩-፲፬፣ ምዕ. ፲፰፥፲፱-፴፫፣ ምዕ. ፳፩፥፩-፫

[8] በሸክኛ ሰማንያ ማለት ሸና፤ ሰው ማለት ደግሞ አሶ ነው፡፡ ሸና አሶ ሰማንያ ሰዎች ማለት ሲሆን በጉዞው ወቅት የኹለቱ ጎሳዎች ሰማንያ አባወራዎችን ለመጥራት ‹‹ሸናሻ›› እንደ ተባሉ ሽማግሌዎች የሚናገሩ ሲሆን ይኽ ዝምድናም በመንግሥት ዕውቅና ተሰጥቶት ከ፳፻ ዐ.ም. ጀምሮ የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት መፍጠር ተጀምሯል፡፡ በርግጥም የቋንቋና የአፈ ታሪክ ግንኙነት እንዳላቸው የካፋ፣ የሸካና የሸናሻ ብሔረሰቦች ሽማግሌዎች ጭምር ተስማምተው የጋራ መድረክ መሥርተው እየሠሩበት ነው፡፡

[9] ከኦሮሞ ሕዝብ ጋር የተደረገውን ጦርነት የታሪክ ምዕራፍ በማድረግ መንግሥት ከበደሌ ወደ ገበር (ያሁኑ ኢሉ አባቦራ ውስጥ ሰሌ ኖኖ አካባቢ) የተዛወረበትን ዘመን መነሻ አድርገው ከገበር በፊት የነበሩ ነገሥታትን ብዛትና ማንነት ሲጠቅሱ በጸሐፍቱ መካከል ልዩነት አለ፡፡ የአጥኚ ቡድኑ ከገበር በፊት ሰባት ነገሥታት እንደነበሩና ጦርነቱም በቱጊ ነቾቺ ዘመን እንደኾነ ሲጠቅሱ የአውግቸው ጥናት ነገሥታቱ ቁጥራቸው ስድስት፣ ጦርነቱም የተደረገው በበዲጋዎቺ ዘመን እንደነበረ ይናገራሉ፡፡ በቃለ መጠይቃችን ወቅት ካገኘነው መረጃ በተጨማሪ በዲጋዎች የተባለው ንጉሥ ጨካኝ እንደነበረና የመናገሻ ቦታ መቀየርም ኾነ አሁን ያለው የብሔረሰቡ አባላት ቁጥር መቀነስ ምክንያቱ ንጉሡ በነበረው ጭካኔ ምክንያት ሕዝቡ ‹‹ላንተ ከምንገዛ ኦሮሞን መስለን ግብር ገብረን እንኖራለን›› ብለው ስለካዱትና ከባሮ ወንዝ በስተደቡብ መቅረታቸው መሆኑን ሥናይ ከገበር በፊት ስድስት ነገሥታት መኖራቸውና ጦርነቱም በበዲጋዎች ንግሥና ዘመን ነው የሚለው የተሻለ አሳማኝ ሆኖ ተወስዷል፡፡

[10] Warner J.Lange፣ “History of the Southern Gonga” P. 123.

[11] ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፤ ‹‹የኢትዮጵያ ታሪክ በግራኝ ወረራ ዘመን››፤፲፱፻፺፪፣ ገጽ ፶፮፡፡

ይህ ሥርዐት በሸካቾዎች ዘንድ በታሪክ ምዕራፍነት ‹‹ቁርፌ ቁዶ›› (የመጉመጥመጥ ሥርዐት) ይባላል። በዚህ አደራና ውሳኔ መሠረት የግራኝ ኀይል እስኪሸነፍ በዱር ቆይተው ወደ ነበሩበት ሠፈራቸው ተመልሰዋል። ከዚህ በኋላ ታሪኩንና ቅርሱን ጠብቆ ምቹ ጊዜን ሲጠብቅ እንደ ኖረ ከመጠቀሱ ውጪ ታቦቶቹን ይዘው ከተቀበሩት ካህናት ሌላ የክህነት ሥራ የሚሠራ ሰው ስለ መኖሩ ወይም የተቋረጠበትን ምክንያትና ዘመኑን በተመለከተ የተገኘ ማስረጃ የለም።

በዘመኑ የነበረውን ጉዳት በተመለከተ ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ሲገልጹ ‹‹በሰሜኑ ክፍል ይህ ጉዳት የደረሰባት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በደቡቡና በምዕራቡ ክፍል ተመሳሳይ ጉዳት ደርሶባታል። በደቡብና በምዕራብ የነበረው የክርስትና ታሪክ በሰሜን ከነበረው የማያንስ ነበረ። … ስለ ደቡብ ክፍል የክርስትና ታሪክ የአቡነ ተክለሃይማኖትን ሐዋርያዊ ጉዞን እንኳ ብንጠቅስ አጭር አይደለም። እርሳቸው የነበሩት በ፲፫ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነው። የመጀመሪያው ሐዋርያዊ ጉዟቸውንም ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ አድርገው ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ማሳነፃቸውን፣ ብዙ ገዳማትን መመሥረታቸውን ገድላቸው ይናገራል። ተልእኳቸውን ፈጽመው በደብረ ሊባኖስ ገዳማቸው በተወሰኑበት ጊዜም በመላው ኢትዮጵያ ፲፪ ደቀ መዛሙርታቸውን ሲያሠማሩ በደቡብና በምዕራብ ኢትዮጵያ ዕጣ የደረሳቸው ብዙ ገዳማትን ሠርተዋል። የክርስቲያኖችን ሕይወትም በክርስቲያናዊ ትምህርት መሥርተዋል።››[12] ብለዋል።[13] ይህም መሠረት የያዘ ክርስትና ከግራኝ በኋላ አለመቀጠሉ ጸሓፊው እንዳሉት ጉዳቱ ምን ያህል ከባድ እንደነበረ ያስረዳል።[14]

[12] በአውግቸው ጥናት ውስጥ የተጠቀሱት የታወቁት የነገሥታት ዘመን ከ፲፱፻፫ ዐ.ም. በፊት እስከ ግራኝ ፫፻፷፭ ዐመት፣ እንዲሁም ዘመናቸውን ማወቅ ያልተቻለውን ለመገመት በአብዛኛው የነገሥታቱ ዕድሜ ከ፻፳ በላይ፣ ንግሥናቸውም እስከ ፺ ዐመት ድረስ ስለ ነበረ የአምስቱ ነገሥታት በዝቅተኛ ግምት ፱ ዐመት ነገሡ ብንል ፬፻፶ ዐመት በድምሩ ፯፻፲ ዐመት ወደ ኋላ ቆጥረን ከ ፲፪፻፹፭ ዐ.ም. በፊት አካባቢ በደሌ ደረሱ ብንል፣ ፲፭ ዐመት ከእናርያው ንጉሥ ጋር የተዋጉበት፣ ከጠቡ በፊትም ሆነ በኋላ ተረጋግተው ንጉሥ ለማንገሥ የፈጀባቸው ዘመን ስለሚኖር፤ በአቡነ ጎርጎርዮስ መጽሐፍ የተጠቀሰውን የጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የስብከተ ወንጌል ዘመን ደግሞ ስናገናዝብ በእርግጠኝነት ከ፲ሥራ ሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በፊት በደሌ አካባቢ ተረጋግተው መኖር እንደጀመሩ መገመት ይቻላል። በየዐመቱ የሚበራው የመስቀል ደመራ ምሰሶ ቅሪት ስለሚጠራቀም እየተቆጠረ የንጉሡ ዘመነ መንግሥት ቊጥር ይታወቅ እንደነበር በጥናታቸው አብራርተዋል። በሕዝቡ ውስጥ ያለውን የኦሪታዊ ሥርዐት ጠንካራነትና የአቡነ ተክለ ሃይማኖትን ክርስቲያናዊ ስብከት ስናገናዝብም አቡነ ተክለ ሃይማኖትና ደቀ መዛሙርቶቻቸው ያስተማሩት ፍልሰቱ አልፎ ከተረጋጋ በኋላ ባይሆን ኖሮ በስብከታቸው ታሪክ ውስጥ የሚጠቀስ የፍልሰት ወይም የብሔረሰቦቹ ግጭት ይጠቀስ ነበረ። በጦርነቱም ሆነ በከባዱ የፍልሰት ማጠናቀቂያና የሠፈራው ሰዐት ለስብከትም ሆነ ሐዋርያዊ ሥራ የማይመች በመሆኑ ይኽን ዘመን ከ፲ሥራ ሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በፊት መውሰዱ ተገቢ ይሆናል። ከዚያም በመቀጠል ስብከተ ወንጌሉ በአቡነ ኢየሱስ ሞዐ መጠናከሩንና የእናርያው ሐዋርያ ስማቸው ዮሴፍ እንደነበረ በገድላቸው ተጽፏል። ከበደሌ በፊት የነበረው ጊዜ የፍልሰት ዘመን መሆኑና በሌላ የኢትዮጵያ ክፍልም የብሔረሰቡ ታሪክ እንደባለርስት አለመጠቀሱ ነው በግርጌ ማስታወሻ ቊጥር ፫ የጠቀስነው የማእከላዊ ኢጣሊያ ጉዳይ ለግምት ቅርብ የሚሆነው። ለሁሉም ግን ሰፊ ጥናት መፈለጉ ግድ ነው።

[13] አባ ጎርጎርዮስ የሸዋ ሊቀ ጳጳስ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፣ ፪ኛ እትም ፲፱፻፸፯፣ ገጽ ፸።

[14] በሸካ ዞን ውስጥ በአንድራቻ ወረዳ ሦስት ቦታዎች ላይ ከግራኝ ሲሸሹ የቀበሩዋቸው አድባራትና ቅርሶች መኖራቸው በግልጽ የሚነገር ሲሆን ከኦሮሞ ሕዝብ ጋር የነበረው ጦርነት ደግሞ ከ፲፯፻ በኋላ መሆኑን ስናገናዝብ ከ፲፭፻፶ እስከ ፲፯፻ ድረስ ስለ ሃይማኖት ትኩረት የተሰጠበት ኹኔታ አልታየም። የዚኽን ምክንያት ማጥናት ያስፈልጋል። ከታሪኩ አንጻር በአኹኖቹ ኢሉ አባ ቦራና ጅማ ዞኖች ውስጥም የሸካውና የሂናርያው የተቀበሩ ሃይማኖታዊ ቅርሶች እንደሚኖሩ የሚጠበቅ ሲኾን የካፋ ሕዝብ እስከ መጨረሻ የጸናው ግራኝ አሕመድ ጎጀብን ተሻግሮ ማጥቃት ባለመቻሉ ይኾናል። እስልምናም ጎጀብን ተሻግሮ ካፋ የገባው በጅማው የኦሮሞ ንግሥና ዘመን መኾኑ ይታወቃል። በአንጻሩም በጦርነት ሰዐት የቅርስ ማሸሹ ተገቢነት እንዳለ ኾኖ በጦርነት ጊዜ ያለውን ክርስቲያናዊ ሕይወት በግልጽ ከማስረዳት ይልቅ ሃይማኖትን ለወንዝ አደራ መስጠት ለምን እንዳስፈለገም ግልጽ አይደለም። ወደፊት እንደምናየው አጽዋማቱንና በዐላቱን አውጥቶ ለሕዝቡ ይነግር የነበረ የባሕረ ሐሳብ ዐዋቂ ምናልባትም መምህርም፣ ወንጌሉን ከዜማው ጋር ያስተምርና ይማር የነበረ ካህን በብሔረሰቡ ዘንድ እንደ ነበረ ስናስብ ደግሞ የዕውቀት ችግር ሳይሆን ሌላ ያልተረዳነው ምክንያት ይኖራል ያሰኛል። ሊሙ/አጋሮ አካባቢ የነበረው የሂናርያው መንግሥት ፈርሶ ሲጠፋ የሸካ ነገሥታት የመናገሻቸውን ቦታ ቢቀያይሩም መንበራቸው ተረጋግቶ እስከ ዐፄ ምኒልክ መንገሣቸው ይታወቃል። ከዚኽ አንጻር የግራኝ አሕመድ ወረራ ጉዳት ከባድ ቢኾንም ሃይማኖትን ለመጠበቅ ቅርሱን መደበቅ፣ እንዲኹም ቀኖና ላለማፍረስ በወንዝ ውኀ መጉመጥመጥን ያስተባበረው የሃይማኖት አመራር (መምህራኑና ካህናቱ) ጭራሽ እስኪጠፉ ያደረሳቸውና ሕዝቡን ዳግም ለማገልገልም ሆነ በየዋሻው የተቀበሩትን ቅርሶችና የተቀበሩትን አድባራት ለማውጣት አለመቻሉ አስገራሚ ምሥጢር ነው። ምክንያቱም ጦርነቱ ፲፭ ዐመት ብቻ ስለ ነበረ ከግራኝ ወረራ በፊት የነበረ ትውልድ በሕይወት እያለ እንዴት ዝም አለ ወይስ ሌሎች ችግሮች ወደዚያም ነበሩ የሚለውን መመርመር ያስፈልጋል። ለዚህም ማገናዘቢያ እንዲሆን በቅርብ የተከሠተውን አጋጣሚ ማየት ተገቢ ነው። በጅማ ዞን ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ እስጢፋኖስ ድጋፍና በሕዝቡ ጥያቄ ገበሬው ራሱ በሰጠው መሬት ላይ ኅዳር ፲፬ ቀን ፳፻፮ ዐ.ም. የተመሠረተው ከጅማ ወደ አጋሮ በሚሄደው ዋና መንገድ ፲፭ ኪ.ሜ. ላይ የሚገኘው የዐለማየሁ ሜጫ አቡነ ሀብተ ማርያም ቅዳሴ ቤተ ክርስቲያን ላይ የተነገረው እውነት ሌላ ጥቆማ ነው። የቤተ ክርስቲያን ግንባታው በኺደት እያለ የአቡኑን መመላለስ ዐይተው ‹‹መጠመቅ እንፈልጋለን›› ብለው የተማጸኑ ፴፯ አባወራዎች እንዲሁም ተጠናቆ ጉልላቱ ሲቀመጥ ደግሞ ‹‹ይህ ምልክት ቀድሞ የእኛ ሃይማኖት ምልክት ነበረ›› ብለው ለመጠመቅ ብዙዎች (ከ፯፻ በላይ የሚሉ አሉ) የአካባቢው ነዋሪዎች (በአብዛኛው ሽማግሌዎች) መምጣታቸውና መጠመቃቸው  የቤተ ክርስቲያን ምልክት የሆነው ጉልላት የቅርብ ጊዜ ትዝታው የሆነ ትውልድ መኖሩን ያስረዳል። ይህም የእናርያ ሕዝብ ክርስትና ጠንካራ የነበረ ስለመሆኑ በሸካ ሽማግሌዎች ከሚነገረውና ከአቡነ ተክለ ሃይማኖት ገድል ጋር ይስማማል። ይኽ የተጠመቀው የሽማግሌዎቹ ትውልድ የትና መቼ ያየውን ጉልላትና መስቀል እንዳስታወሰ ግን ቢጠና መልካም ነው።

የሸካቸው ንጉሥ መናገሻ ከበደሌ ወደ ገበር ከዚያም በተለያዩ ጦርነቶችና (በአብዛኛው ከኦሮሞ ጋር የተደረጉ ናቸው) ችግሮች ሲዘዋወር ቢቆይም ዝርዝሩ ግን በማስረጃ አልተገኘም፡፡ የዳግማዊ ምኒልክ የማስገበር ታሪክ የመጣው የሸካቸው ንጉሥ በአሁኑ አንድራቻ ወረዳ በሚገኘውና የቤተ መንግሥቱ ቅሪት ወደ ሚገኝበት የአንድራቻ ተራራ መንበሩን ካመጣ በኋላ ነው፡፡ በ፲፱ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ዳግማዊ ምኒልክ በደቡብና በምዕራብ ክፍለ ሀገራት የሚኖሩ ብሔር ብሔረሰቦችን ለማስገበር በአደረጉት እንቅስቃሴ ከሸካቾ ንጉሥ ጋር ተዋግተዋል፡፡ በተደረገው የመልእክት ልውውጥ የሸካቾ ንጉሥ ለመገበር ይስማማሉ፡፡ ከስምምነቱ በኋላ በወቅቱ የጦሩ መሪ ራስ ተሰማ ናደው ወደ ዐድዋ እንዲዘምቱ ሲጠሩ በቦታው ጥቂት ሠራዊት ትተው ይሄዳሉ፡፡ ይህንን እንደመልካም አጋጣሚ በመጠቀም ሕዝቡ በቦታው የነበሩትን የንጉሡን ሠራዊት አባላት ፈጃቸው፡፡ ድርጊቱንም ከዐድዋ ድል በኋላ የምኒልክ ሠራዊት ከምርኮ በአገኘው የጦር መሣሪያ በመታገዝ የሸካቾን ሕዝብ ተበቀሉት፡፡ ሽማግሌዎች እንደ ሚሉት ከሸካቾ የተማረከውን ሰልበው ወደ ንጉሡ ሲያቀርቡ የተገረዘ መሆኑን አይተው የግርዛቱ ምክንያት ክርስትና ነው በሚል የጌጫ አቡነ ሐራ ድንግልን ታቦት አምጥተው አክብረውታል፡፡ በ፲፱፻፴፰ ዐ.ም. በጅሮንድ ተምትሜ በተባሉ የመንግሥት ተወካይ አስተባባሪነት ታሪኩን በማጥናት፣ ቀድሞ አደራ ከሰጡት የአኢአች ወንዝ የሀገር ሽማግሌዎችና ቀሳውስት በተገኙበት ከወንዙ ውኀ ተጉመጥምጠው ወደ ወንዙ በመትፋት የሰጡትን አደራ መልሰው ተረክበዋል ተብሎአል፡፡[15] ከዚያ በኋላ ሕዝቡ በባህሉ የሚያውቀው ሥርዐተ አምልኮ ቀድሞ ወደ ነበረበት ክህነታዊ ሥርዐት አለመመለሱን በተግባር ሥናይ በበጅሮንድ ተምትሜ ጅምር የቀጠለው ሐዋርያዊ ሥራ እንዳልተሠራና ዐላማውም ፖለቲካዊ ብቻ እንደ ነበረ መረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ በኋላ ያለው ዘመናዊነትና ፕሮቴስታንትነት ባህሉን እያስረሳው መጣ፡፡ ይህንን ታሪክና ባህል የሚያውቀውና ይኖርበት የነበረው ሕዝብ ቍጥርም ተመናመነ፡፡

## ፩.፩ የጥናቱ አስፈላጊነትና ጠቀሜታ

ባለንበት ዘመን ስለ ሃይማኖት ጉዳዮች እውነታን የሚጠቁሙ መነሻዎችን ብቻ ይዞ ከመናገርም ሆነ ከመሥራት ይልቅ ሣይንሳዊ አመክንዮዎችን መጠቀሙ አስፈላጊ ነው፡፡ ከዚህም በላይ ተግዳሮት ላለባት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ይህን ማድረግ ግዴታዋ ነው፡፡ ይልቁንም የእምነት ተቋማት በዐይነትና ስያሜ እየበዙ የመጡበትና አንዳንዶቹም ቤተ ክርስቲያንን የጥቂት ክፍሎች ወይም ዘውጎች አድርጎ ለመሳል ሓላፊነት የጎደለው አካሄድ የሚታይበት ዘመን መኾኑ የጥናቱን አስፈላጊነት ያጎላዋል፡፡ ምእመናንን የሚለያየውን ምድራዊ ዘውግ አሽንፎ ወደ ሰማያዊው የቅድስና አንድነት ለመጥራት ጥርጊያውን በማቅናት በኩል እንደዚህ ዐይነት ጥናት ሰፊ ጠቀሜታ አለው፡፡ ዋነኛ ጠቀሜታውም ምእመኑ በቀላሉ የሚረዳቸውን ተጨባጭ ሐቆች ለይቶ ማቅረብ መቻሉ ነው፡፡ ከዚህም ባሻገር የቤተ ክርስቲያን የአስተዳደርና የክህነት አገልጋዮች ለሚሠሩት ሥራ አስረጅ የሚሆኑ ጭብጦችን በጥናቱ ማግኘት ያስችላል፡፡ ተመሳሳይ ጥናቶች በሌሎችም ብሔሮችና ብሔረሰቦች ሊሠሩ ከቻሉም የጥናቶችን አማራጭ ማለትም ሃይማኖትን በብሔሮችና ብሔረሰቦች ታሪክ፣ ባህል፣ ቋንቋና የቀን አቆጣጠር ውስጥ መፈለግ እንደሚቻል ያስገነዝባል፡፡ በተጨማሪም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ከጊቤ ወንዝ ማዶ የነበራትን መሠረት መነሻ በማድረግ ለምእመናን ማድረስ የሚገባትን አገልግሎት በአግባቡ እንድትቃኝ ያነሣሣል፡፡

## ፩.፪ የጥናቱ ዐላማ

የጥናቱ ዋና ዐላማ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ያላትን አሻራ ከሸካ ሕዝብ ታሪክ፣ ባህል፣ ቋንቋና የቀን አቆጣጠር ውስጥ መፈለግ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በተለያዩ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ውስጥ መሠረት እንዳልነበራትና በቅርብ ዘመን የነገሥታትን ፈቃድ ለመፈጸም በግድ እንደተጫነችባቸው በየአደባባዩ ይዘገባል፡፡

[15] ላንጌ፣ ገጽ ፻፳፬፡፡

ይህ እውነት አለመሆኑን[16] ማረጋገጥ ሌላኛው የዚህ ጥናት ዐላማ ነው። በአንጻሩም የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሃይማኖት መሠረቶች የሚባሉት የትምህርትና የአምልኮ ቦታዎች (አብነት ትምህርት ቤቶችና ገዳማት) በሸካ አካባቢ ተስፋፍተው ባይገኙም የቤተ ክርስቲያኒቱን አሻራ በሕዝቡ ውስጥ መፈለግ የጥናቱ ዐላማ ነው። በሌሎች የሀገሪቱ ታሪኮች የተጠቆሙትን የአካባቢውን የክርስትና ታሪክ አጥንቶ መለየትና ተጨባጭ ማስረጃ ማዘጋጀት ወይም ሌሎች አጥኚዎችን የሚያግዙ አቅጣጫዎችን ማሳየት ጥናቱ ዐላማ ካደረጋቸው መካካል አንደኛው ነው።

## ፩.፫ ውስንነት

በሀገራችን ታሪክ፣ ባህልና ቋንቋ ላይ ትኩረት በማድረግ ለማጥናት የመረጃ ምንጮቹን አመሳክሮና አገናዝቦ ለማቅረብ የጽሑፍ ምንጮቹ በቂ የሚባሉ አይደሉም። ስለዚህም በዚህ ጥናት ሊነሡ የሚችሉ ሰፊና ጥልቅ ጉዳዮች ቢኖሩም የጽሑፉን ይዘት ለተጠቃሚው በቂ መነሻ ለመስጠት በተለይም የሚመለከታቸው የቤተ ክርስቲያንም ኾኑ የተለያዩ ዘርፎች ምሁራን ጥናትና ግምገማ እንዲያደርጉ ለማነሣሣት የሚጋብዝ እንዲኾን ብቻ ተሞክሯል። ለዚህ ጥናት በምንጭነት የተጠቀሱት ሥራዎች ሣይንሳዊ የምርምር ዘዴን አሟልቶ አለመገኘት አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል። እንደዚሁም ይኽ ዐይነቱ ጥናት ሣይንሳዊ ምርምርን በሚከተሉ የታሪክ፣ የቋንቋ፣ የባህልና የቅርሳ ቅርስ ባለሙያዎች በተናጠል ወይም በኅብረት አለመከናወኑ የሚፈጥረው የአቅም ውስንነት አለ። በጊዜና በአቅም ውሱንነት ምክንያት ሁሉንም የሸካቾ ባህላዊ ክንዋኔዎች በመመርመር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ክርስትናን አሻራ ለማሳየት አልተቻለም። ይህ አለመኾኑ በጥናቱ ውጤት ላይ ተጽእኖ ይኖረዋል።

## ፩.፬ የጥናቱ አዘጋገብ ዘዴ

ለዚህ ጥናት የሚያስፈልጉት መረጃዎች የተሰበሰቡት ከቀደምት ጥናቶችና ከመስክ ነው። ከቀደምት ጥናቶች መካከል በብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ መጽሐፍ[17] ላይ የተጠቀሱት የአካባቢው ሃይማኖት ቅሪቶች ጥሩ መነሻ ሆነዋል። እንደዚሁም ጀርመናዊው የማኅበረሰብእ ሣይንስ ምሁር በጻፉት መጽሐፍ[18] የብሔረሰቡን ታሪክና ባህል በስፋት ከማተት አንጻር ብቸኛ መጽሐፍ ነው። ምሁሩ በሣይንሳዊ ምርምር ለመጻፍ ጥረት አድርገዋል። ሆኖም የመረጃ እጥረት እንዳጋጠማቸው ከመጽሐፉ ይዘት መረዳት ይቻላል። የብሔረሰቡን ታሪክና ባህል እንዲሁም የአካባቢውን ቋንቋ የሚያውቅና የሚያግዛቸው በቂና ብቁ አካል ባለማግኘታቸው በጥያቄነት ሊነሡና በስሕተትነት ጭምር ሊነገሩ የሚችሉ መረጃዎችን በመጽሐፋቸው አካተዋል። ይኽም በየክፍሉ አስተያየት ተሰጥቶበታል።[19] ለዚኽ ጥናት ሰፊ ግብዐት የሆነው በብሔረሰቡ ባህልና ትውፊት ላይ የሚያተኩረው የአውግቸው ወርቅ አገኘሁ (፲፱፻፺፬) ያልታተመ ጥናት[20] ነው። ይኽ ጥናታቸው ከፍተኛ ተቀባይነት አለው።

ከላይ የተገለጹትን ሥራዎች ትክክለኛነት ለማመሳከር ትልቁን ድርሻ የወሰዱት የሸካቾ መንግሥት የመጨረሻ መናገሻ በነበረችው አንድራቻ የሚኖሩ የብሔረሰቡ ታሪክና ባህል ዐዋቂ ሽማግሌዎች ናቸው። ብዙውን ጊዜ የሕዝብ ውክልና ያላቸው የሀገር ሽማግሌዎች ስለ ሕዝቡ ማንነት የተሻለ ጥናት ያደርጋሉ።

[16] ዋቅቤካ ኤርፓ የኦሮሞ ብሔር ባህል ሥርዐተ አምልኮ እና የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቁርኝት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጥናት መጽሔት (፳፻፬) ገጽ ፳፯-፶፫

[17] አባ ጎርጎርዮስ የሸዋ ሊቀ ጳጳስ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፣ ፪ኛ እትም ፲፱፻፸፯፣ ገጽ ፸።

[18] ዎርነር ጄ. ላንጌ ‹‹The History of Southern Gonga›› (19)

[19] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ ፪።

[20] አውግቸው ወርቅ አገኘሁ፤ ባህልና ትውፊታዊ ክንዋኔዎች በሸካቾ (፲፱፻፺፬) ያልታተመ

ስለ ብሔረሰባቸው የሚሰጡት ማስረጃም ከፍተኛ ተቀባይነት አለው፡፡ በዚሁ መሠረትም በአውግቸው ጥናት ውስጥ የተካተቱት መረጃዎች ትክክለኛነት በሽማግሌዎቹ ተረጋግጠዋል፡፡ መናገሻ በነበረችው አንድራቻ ወረዳ የሚኖሩ የመጨረሻው የንጉሥ ቤተሰቦች፣ የቃልቻ (ቡለፎ) ተዋናይ ወገኖች፣ እንዲሁም በችግር ወቅት ተቀበሩ የተባሉትን ቅርሶች ጭምር እየተመካከሩ የሚጠብቁት እነዚሁ የአንድራቻ ወረዳ ሽማግሌዎች ናቸው፡፡

ለዚኽ ጥናት የሚረዱ መረጃዎች ከሀገር ሽማግሌዎች የተሰበሰቡት በድምፅና በምስል ቀረጻ በማድረግ ነው፡፡ የሀገር ሽማግሌዎች በሰነድ ሊቀመጥ የሚችል መረጃ እየሰጡ መኾናቸውን በመገንዘብ በተወሰኑ ርእሰ ጉዳዮች ላይ ለሚቀርብላቸው ጥያቄ መክረውና የሐሳብ ልዩነታቸውን በውይይት ወደ አንድ አጠቃለው ለመረጃ ጠያቂው ይናገራሉ፡፡ የየግል መረጃቸውን በተናጠል አልነገሩም፡፡ በጋራ አንድ ወጥ ሐሳብ በመስጠታቸው ምክንያትም በምንጭነት ሲጠቀሱ ሽማግሌዎች ተብሎ ነው፡፡ በድምፅና በምስል የተሰበሰቡት መረጃዎች ለዐውደ ርእይ በሚያመች መልክ ተቀናብሮ ከጳጉሜ ፩-፫ ቀን ፲፱፻፺፯ ዐ.ም. በማሻ ከተማ ታከለ አዳራሽ ከሌሎች የቤተ ክርስቲያን ርእሰ ጉዳዮች ጋር በዐውደ ርእይነት በቀረበበት ጊዜ አብዛኛዎቹ ሽማግሌዎች ተጠርተውና ተገኝተው የጥናቱን ተገቢነት መስክረዋል፡፡ ዋና ዋናዎቹ ሽማግሌዎችም ዶ (አቶ) ኦጎ ኒቸራሻ - አስተባባሪ፣ ዶ አድነው ደስታ- ዕድሜ ፸፱፣ ዶ አዛጌ አምበሎ - ዕድሜ ፶፯፣ ዶ ጋውስራሻ አምበሎ - ዕድሜ ፸፯፣ ዶ እሸቱ ኒፈራሻ ናቸው፡፡

ለሸካ ዞን አስተዳደር ምክር ቤት የቀረበውና በስድስት የምሁራን ቡድን እና በኹለት አማካሪዎች በ፲፱፻፺፬ ዐ.ም. ጥር ወር የተደረገው ጥናት ሌላው ግብዐት ነው፡፡ አቶ ተሾመ ኀይሌ (በምጣኔ ሀብት የመጀመሪያ ዲግሪ)፣ አቶ አበራ ገሊቶ (በሥነ ሕይወት ዲፕሎማ)፣ አቶ ጀመረ አምቦ (በአስተዳደር ዲፕሎማ)፣ አቶ አምበቻ ሻዎ (በቋንቋ ዲፕሎማ)፣ አቶ ቴዎድሮስ ደይኖ (በጂኦግራፊ ዲፕሎማ) ዋናውን የጥናት ሥራ እያከናወኑ አቶ ብርሃኑ ዘለቀ (በሕግ የመጀመሪያ ዲግሪና በወቅቱ ዋና አስተዳዳሪ) እና አቶ በቀለ አጦ (በኬምስትሪ የመጀመሪያ ዲግሪ) (የትምህርት ደረጃቸው በ፲፱፻፺፬ የነበረ ሲኾን በአሁኑ ወቅት ብዙዎቹ ኹለተኛ ዲግሪ ሠርተዋል) ያማከሯቸው እንደነበረ የጥናት ሰነዱ ያመለክታል፡፡ ጥናቱ የተከናወነው በወቅቱ የነበረውን አስተዳደራዊ ጉዳዮች ለማገዝ ቢኾንም በውስጡ የያዘው ታሪክና ባህል ነክ ጉዳዮች ለዚኽ ጥናት አስፈላጊ በመኾኑ ቀጥታ ተጠቅመንበታል፡፡ ምናልባትም ኹሉም ምሁራን በዞኑ አስተዳደር ሥራዎች ላይ ቀጥተኛ ተሳታፊ ስለነበሩ ቃለ መጠይቅ ያደረጉላቸው የሀገር ሽማግሌዎች ማንነትና ከዐፄ ምኒልክ ዘመን ጀምሮ የነበሩትን መንግሥታዊ ሰነዶች በስፋት መመርመራቸው ጥናቱ ሌሎቹን ምንጮች ማረጋገጫም መኾን ይችላል፡፡

## ፮. የባህልና የሃይማኖት ቁርኝት በሸካቾ

ባህልና ሃይማኖትን በአንድ ርእስ ሥር ማየት ያስፈለገው በመግቢያው ላይ እንደ ተገለጸው በሰው ልጅ ሕይወት፣ አመለካከትና አስተሳሰብ የእምነቱ አሻራ መኖር መቻሉና ይኽም በአለባበሱ፣ በአነጋገሩና ማኅበራዊ ግንኙነቱ ላይ የሚገለጥ መሆኑ ነው፡፡ በዚኽም መሠረት የሸካቾ ሕዝብ አስቀድሞ በነበረው ሃይማኖታዊ አስተሳሰብና አመለካከት ምክንያት በአዳበረው በባህሉ ውስጥ ያለውን ሃይማኖታዊ አሻራ በአግባቡ መመርመር የዚኽ ክፍል ትኩረት ኾኗል፡፡ ኹሉንም ባህላዊ ክንዋኔዎች ለማየት ዐቅምና ጊዜ በመገደባቸው ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ክርስትና እምነት ጋር የጎላ ተመሳስሎ የሚታይባቸውን ሦስቱን ብቻ ቀጥለን እናያለን፡፡

**ዲጎ (ሰላምታ)**፡- በማንኛውም ጊዜ የተገናኙ ሁለት ሰዎች ተራ በተራና በድግግሞሽ ጉንጭ ላይ መሳሳም መደበኛ ሰላምታ ሲሆን የሚለዋወጧቸው ቃላትም በአብዛኛው ሌላውን ማፍቀርን በመግለጽ ራስን የሚረግሙ ናቸው፡፡ ብዙዎቹ ሰላምታ ተለዋዋጮች ‹‹የሪስ ጋሰቶ ብደ›› (ለአምላክ ምስጋና ይድረስ) የሚሉበት ጊዜም አለ፡፡ ራስን በመርገም ከሚነገሩት ውስጥም ‹‹ይኖ ታ የሺ›› (ሰይጣን እኔን ይጉዳኝ) የሚልና መሰል በሃይማኖታዊ መሠረት ላይ ብቻ የሚያተኩሩ የሰላምታ አባባሎች አሉ፡፡[21] በሰላምታ መለዋወጥ ውስጥ የሚታየው ነገር በቃላቱም ይሁን በአባባሉ የአንዱን ፈጣሪ መኖር ብሎም መልካሙን እንዲያደርግ ለወዳጁ የሚመኝና ክፉ የሚያደርግ ርኵስ መንፈስ መኖሩን የሚገልጥ ነው፡፡ በተቃራኒው ደግሞ በሃይማኖት የማይመስለውንና ባህሉን የማያከብርለትን ሰው በመሳሳም ሰላም አይለውም፡፡ እንዲያውም የራሱ የሽካቾ ብሔረሰብእ አባል ኾነው በአመጋገባቸው አንድ ያልሆኑትን የመንጃ ጎሣ አባላት እስከዚኽ ዘመን ድረስ ከማኅበራዊ ሕይወት ጭምር በማግለል ከሌሎች የሽካቾ ጎሣዎች ተለይተው የራሳቸውን መንደር መሥርተው እንዲኖሩ ተጽእኖ አድርጓል፡፡ ወደ ሃይማኖተኛው ሽካቾ (ባይጠመቅም ‹‹ክርስቲያን ነኝ›› ይላልና) ቤትም እንዲገቡ አይፈቀድም፡፡[22] የጋራ ጉዳይ ሲያጋጥማቸውም (ጦርነትን ጨምሮ) የሚተባበሩት ድርሻ ተከፋፍለው በአካል ተራርቀውና ሳይነካኩ ነው፡፡

**ማዩ ማዮ (አመጋገብ)**፡- በሽካቾ ብሔረሰብ የአመጋገብ ባህል ውስጥ ግልጥ ኦርቶዶክሳዊ ትውፊት ይታያል፡፡ ከምግብ ዐይነትም የቆጮን፣ የሥጋን፣ የወተትንና የጥራጥሬ ዘሮችን በብዙ ዐይነት አዘጋጅቶ ይመገባል፡፡ ማዕድ የሚቀረበውም በዕድሜና በማዕረግ በመከፋፈል ነበር፡፡ ፋና ወጊ (መብራት ይዞ የሚያበላ) የነበረ ሲሆን የቀረበውን ማዕድ ከመካከላቸው ትልቁ ሽማግሌ ‹‹መሽመአፍ ቅዱሩሼ፤ ማራኮ ሺቻላ፤ ይኖ ሀንጎዴሊቤ›› (በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ መላእክት ይቅደሙ፤ ሰይጣን ይወገድ!) ብሎ በመባረክ ቆጮውን ቆርሶ ለአንዱ ይሰጣል፡፡ መጀመሪያ ተቆርሦ የተሰጠውም አጠገቡ ላለው ሌላ ሰው ይሰጣል፡፡ አንዱ ለሌላው እየሰጠ ለሁሉም የማዕዱ ተሣታፊዎች ይዳረሳል፡፡ መጀመሪያ የባረከው ሰው ለኹሉም አያደርስም፡፡ ምግቡን በሥላሴ ስም መባረኩ ከክርስቶስ መወለድ በኋላ የታወቀ ግልጥ ክርስትና መኾኑንና ቆርሶ መስጠቱም የዘመናት ብዛት የቀየረው ሥርዐት እንዳለ ኾኖ ክህነታዊ ቡራኬ ነበረ የሚያሰኝ ነው፡፡ ማዕዱ ከተጠናቀቀ በኋላም ‹‹ዲሮ›› (ምርቃት) ያለ ሲሆን ቢያንስ ሦስት ታላላቅ ሰዎች ሲመርቁ የተመገበው ኹሉ የገበታውን ጠርዝ በቀኝ እጁ ይይዛል፡፡ ምርቃቶቹም የፈጣሪን በረከት ለቤቱ የሚመኙ ናቸው፡፡ ‹‹የሪ ኢምባ (እግዚአብሔር ይስጥልኝ)፣ ሃኒ ማምኒ ኖሲ ፈኒቤ (የእህል በረከት ይስጠን)፣ ኖሽምሲ ቢዮዮሄ (በሽታ ከሕዝባችን ይራቅ) … ወዘተ›› የሚሉት ምርቃቶች ዐይነተኛ ምሳሌ ናቸው፡፡

የሚበላና የማይበላ ምግብ የሚመርጡት በመጽሐፍ ቅዱስ ከተገለጸው ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ኦሪት ዘሌዋውያን ፲፩ የተጠቀሰውን የአመጋገብ ሥርዐት በሐዲስ ኪዳኑ የሥርዐት መጽሐፍም ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፳፫ የተዘረዘሩትን ለይቶ ከመንጃ ጎሣ በቀር በኹሉም የብሔረሰቡእ አባላት ሲተገበር መቆየቱ ጠንካራ ኦርቶዶክሳዊ ተዋሕዶ የሃይማኖት መሠረት ካልኖረ የማይቻል ነው፡፡ ሌሎች የሽካቾ ጎሣዎች መንጃዎችን የማግለላቸው ምክንያት የማይበላና የሚበላ ብለው ባለመለየታቸው እንደሆነ ይነገራል፡፡ በጦርነት ወቅት ሁሉም የሽካቾና የመንጃ ጎሣዎች ተስማምተው ያገኙትን ይበላሉ፡፡[23]

---

[21] በ፲፱፻፹፭ ዐ.ም. በመዠንግርና ሌሎች ብሔረሰቦች መካከል የተከሠተውን ግጭት በሚመለከት በሕፃናት ጭምር ይዜም የነበረው ዘፈን ሃይማኖታዊ አመለካከቶቹ ሥር መስደዳቸውን ያረጋግጣል፡፡ ‹‹ቴፒ ይኖ ጊየ፣ መሰንጎ ኮዬቤ›› ትርጕሙም ሰይጣን ቴፒ ገባ፣ መዠንግሮችን ጦር አስነሳባቸው ማለት ነውና፡፡ ይኸም ሐሳብ ሰላም ከእግዚአብሔር፣ ጸብ ደግሞ ከሰይጣን እንደሚገኝ መታመኑን ይገልጻል፡፡

[22] ከቤቱ እንዳይገቡ አንዱ ወገን አለመፍቀዱ በከተማ መጠጥ ቤቶችና ሱቆች ድረስ የዘለቀ ነው፡፡ የመንጃ ጎሳ አባላት የገቡበትን የከተማ ሱቅም በሌላው ወገን ይገለል ወይም ይወቀስ ነበር፡፡ ይኽ አመለካከት እንዲስተካከል በመንግሥት ጥረት በመደረጉ የተወሰነ ለውጥ ይታያል፡፡ በመንግሥት ሥልጣን ውስጥ ከመንጃ ጎሳ አባላት ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ አመራር (ከወረዳ እስከ ዞን) በመሾማቸውም በግድ የሚደረጉግ ኀኙነቶች እየተፈጠሩ ነው፡፡ በዚኽ ረገድ ዘመናዊ አመክንዮዎችም ተጨምረውበት እየተሻሻለ እየኼደ ነው፡፡ ለሰላምታም ቢኾን መጸያየፉ ጭራሽ ጠፋ ማለት ግን አይቻልም፡፡

[23] አውግቸው፣ ገጽ ፲፱-፳፯ እና ፳፪-፳፫፡፡

ነገር ግን፣ ከጦርነት በኋላ የሸካቾ ጎሣዎች ወደ ቀድሞ የሚበላና የማይበላ ብሎ የመምረጥ ተግባራቸው ሲመለሱ የመንጃ ጎሣ አባላት ግን ያገኙትን መብላት ይቀጥላሉ፡፡ ይህም የመንጃ ጎሣ አባላት እንዲገለሉ አደረገ ይባላል፡፡[24]

**ሹዎ (ሴቶችና ወሊድ)፡-** በሃይማኖት ትምህርት ውስጥ ከፍተኛ ቦታ ከተሰጣቸውና ሥርዐት ከተሠራላቸው ጉዳዮች መካከል መንጻት እና ድኅረ ወሊድ የሚሉት ይጠቀሳሉ፡፡ በሸካቾ ባህል የሴቶች የመንጻትና የድኅረ ወሊድ ሥርዐቶች የተለየ ትኩረት ይሰጣቸዋል፡፡ በአውግቸው ጥናት በስፋት እንደተጠቀሰው ሴት የወር አበባዋን የምታይበትን ቀን ቆጥራ ለዚኽ ተብሎ ወደተሠራ ጎጆ (ከዋናው ቤት ተያይዞ የተሠራ ሊሆን ይችላል) መግባት ይጠበቅባታል፡፡ በዚኽ ቤት ለሰባት ቀን ስትቆይ የምትነካው ይረክሳል ተብሎ ስለሚታመን የምትመገበው በተለየ ዕቃ ወይም በቅጠል ነው፡፡ ኦሪት ዘሌዋውያን ላይ የሕጉ መሥራች ሙሴ ሲጽፍ ‹‹ሴት ብታረግዝ፣ ወንድ ልጅም ብትወልድ ሰባት ቀን ያህል የረከሰች ናት፤ እንደ ሕመምዋ መርገም ወራት ትረክሳለች … ከደምዋም እስክትነፃ ሠላሳ ሦስት ቀን ትቀመጥ፤ የመንጻትዋ ቀንም እስኪፈጸም ድረስ የተቀደሰን ነገር አትንካ፤ ወደ መቅደስም አትግባ…›› ያለውን የሸካቾ ባህል ከሚተገብረው ጋር መመሳሰሉን መረዳት ይቻላል፡፡ እንደዚኹም የመውለጃዋ ጊዜ ሲደርስ ከሰውነቷ የሚወጣውን ፈሳሽም ሆነ ምናልባት በወሊድ ላይ ሕፃኑ ወይም እናትየው ቢሞቱ ቤቱ እንደረከሰ ስለሚቆጠር ወልዳ ለ፵ ቀን የምትቆይበት ‹‹ሹዌከሮ›› (የመውለጃ ቤት) ይሠራላታል፡፡ ምጥ እንደ ጀመራት በቅርብ የሚከታተልዋት ባለቤት ዋና አዋላጅዋ ወደዚኽ ቤት ያስገቧታል፡፡ ይኽም በመጽሐፍ ቅዱስ ከተጠቀሰው የመንጻትና ርኵሰት ትምህርት እንዲኹም በሐዲስ ኪዳን ከተሠራው የመንጻት ሥርዐት ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡

ከዚኽ በተጨማሪ በወሊድ ምክንያት የሚያገኙትን ደስታ የሚገልጹበት አነጋገር ሃይማኖታዊ መሠረት አለው፡፡ በወሊድ ምክንያት ለ፵፹ ቀናት በሚቆዩባቸው ጊዜያት የደስታ ስሜታቸውን የሚገልጹባቸው አባባሎች በቋንቋው መደበኛ ከመኾን አልፈው የሥነ ቃል ክፍል መኾን ችለዋል፡፡ በኦርቶዶክሳውያን ዘንድ በወሊድ ጊዜ የቅድስት ድንግል ማርያምን ርዳታዋን መፈለግ የተለመደው ነው፡፡ ለተራዳኢነቷም ምስጋና ማቅረብ፣ በዘፈንና በመልካም ምኞታቸው ውስጥ እሷኑ ማወደስ ሃይማኖታዊ መሠረት አለው፡፡ ይኽን ስሜት በአባባልና በዜማ ማቅረብ ለተጠመቀ ሰው ብቻ የሚተው አለመኾኑን ከሸካቾ ብሔረሰብእ ባህል እንረዳለን፡፡ የሸካ ብሔረሰብእ አባል በመሆን ብቻ የሚያደርገው እንጂ ከአባባሎቹና ከሥነ ቃል ሀብቶቹ በጥቂቱ መጥቀስ ሀሳቡን ግልጽ ያደርገዋል፡፡

ሴት ስትወልድ ጠያቂዋ ‹‹ዋማ ታገኔ ማራሚ ኔ ቢችታኔ›› (እንኳን እመቤቴ ማርያም በሰላም ፈታችሽ) ስትባል እርስዋም ‹‹ዲጎና ቢችያታኔ ማራሚ ዎቶ ዲተዎ›› (በሰላም ተፈትቻለሁ፤ የማርያምን ሥራዋን/ተአምሯን እናገራለሁ) ትላለች፡፡ በታላቅ እንክብካቤ ለ፵ ቀናት ከቆየች በኋላ ደግሞ ፵ኛው ቀን ‹‹ወሾ›› (የማንጻት ቀን) ተብሎ ደማቅ ሃይማኖት ነክ ሥርዐት ይፈጸማል፡፡ ይህ ሥርዐት የሚፈጸምበት ዕለት በርኵሰት ሥጋት ወደ ተወችው ዋናው ቤቱዋ የምትገባበትና የትዳር ኑሮዋን ዳግም የምትጀምርበት ነው፡፡ የቀናቱ ብዛት ፵ መኾኑና በ፵፩ው ቀን ወደ ቤቷ መግባቷ ምናልባት በኦሪት ዘሌዋውያን ፲፪፥፬ ‹‹ከደምዋም እስክትነጻ ለሠላሳ ሦስት ቀን ትቀመጥ›› ያለውን ይዘው ይሆን? ያሰኛል፡፡ ከወለደች ከሠላሳ ዐራተኛው ቀን በኋላ የ‹‹ማንጻት›› ሥራው ለዐራት ቀን በሚቆይ ዝግጅት ላይ ዘመድ ተጠርቶ ይጋበዛል፡፡፡ በዚኽም ላይ የ፵ ቀናት ቆይታዋ በሥነ ቃልና በጭፈራ ይገለጻል፡፡[25]

[24] ዘሌ ፲፪፥፩-፰

[25] በዚኽ ላይ በአውግቸው ጽሑፍ ገጽ ፺፰-፻፬ በስፋት የተገለጸውን ይመልከቱ፡፡

ከሰው አጠራሩ እንኳ ጥቂት ብንጠቅስ ሚስት ‹‹ኢቶ ዋቴና ደንቦ ወቺበኔ - ኑልኝና የማርያምን ገመድ ወደ ማርያም ልመልሰው››፣ ብላ ስትጠራቸው ተጠሪዎቹም ‹‹ኢንዶኤ ኔ ኤሪሞቺ ኖ ኤርሞሊ አከተ ቀጂዎቺ የሪኖ ደጊቤ - ደስታሽ ደስታችን ነውና እግዚአብሔር ጤና ይስጠን እንገኛለን›› ሲሉ ባልም በበኩሉ ‹‹ወኔሸኖባ ወቤ ኡሬ ወደሮ ወቺባኔ፤ ኢቴና አሮባ ኢኪ ኮተቦኔ - ሰኞ ዕለት ገመዱን ስለምንመልስ ኑና ከእኛ ጋር ተቀመጡ››፤ ሲላቸው ተጠሪዎቹ ደግሞ ‹‹ኢንዶኤ የሪኖ ዲገቤ - እሺ እግዚአብሔር ጤና ይስጠን›› በማለት ይመልሳሉ። በመጨረሻም ወገብዋን የምታስርበት ‹‹ሹዌወዳሮ›› (የወሊድ/የማርያም ገመድ) ተፈቶ በማርያም ጋን ‹‹ማራሚ ጋኖ›› ላይ ታስሮ ‹‹ለማርያም አስረከብኩኝ›› የምትልበት፣ በማሰሮው የተሞላውን ጠላ ቀድማ በመቅመስ (የግድ ነው) ‹‹ማራሚ ወልፋ›› (በማርያም ስም ባርኬዋለሁ) ትላለች፡፡ ከዚያ በኋላ ሌሎችም ‹‹አሜን ወልፋ›› (አሜን ይባረክ) ብለው ይቀምሱታል፡፡ በዚኽ ሥርዐትም የወለደችው ሕፃንና የእርሷ ማሕፀንም ለወደ ፊት ይባረካል ተብሎ ይታመናል፡፡ በመጀመሪያው ቀን አራሷን ይዘው ወደ ዋናው ቤት የሚገቡት ዐራት ጊዜ በመዞር ነው፡፡ እዚኽ ላይ ቤቱ የሚዞረው ዐራት ጊዜ ከመሆን በቀር ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ‹‹ንስእለኪ ማርያም እያሉ የተዘጋ ቤተ ክርስቲያን ዞረው ይኼዳሉ›› ያሉትና በዑደት መባረክን መጽሐፋዊ ባህል ካደረገችው ቤተ ክርስቲያን ትውፊት ጋር ይመሳሰላል፡፡ ይህም የሸካቾና የቤተ ክርስቲያንን ዝምድና በተጨማሪ ያስረዳል፡፡ ለዐራት ቀን የማርያም ጋን ነቀላ የሚከናወነው ለድንግል ማርያም በጭፈራ መልክ ልመና በማቅረብ ነው፡፡ ዘፈኑም ድንግል ማርያምን ከፍ ከፍ ያደረገና ስጦታዋን መሻትን በመለማመጥ መጠየቁ ኦርቶዶክሳዊነቱን ያረጋግጣል፡፡ አንዱ ሲመራ ሌላው በመቀበል የሚካሄደው ዘፈንም የሚከተለውን ይመስላል፡፡

| **አውራጅ** | **ተቀባይ** |
| --- | --- |
| ‹‹ታገኔኔ ወታ ምቤ›› (እመቤታችን ተመልሰሽ ነይ) | ‹‹ታገኔኔ ወታ ምቤ›› |
| ‹‹ነምቶሶ ናኦ ዴቤ››(ስትመለሽ ለታምርሽ ወንድ ልጅ ይዘሽ ነይ)፣‹ | ‹ታገኔኔ ወታ ምቤ›› |
| ‹‹ነምቶሶ ናኤ ዴቤ›› (ስትመለሽ ለታምርሽ ሴት ልጅ ይዘሽ ነይ) | ‹ታገኔኔ ወታ ምቤ›› |

አውራጅ ሲደረድር እድምተኛው በየስንኙ መካከል ይቀበላል፡፡ ከአዛውንቱ አንጋፋው ‹‹ያፊ ያጢሹየሞ ሹቤ›› (እንደ ቁልቋልና እንጨት ዘራችሁ ይብዛ) ሲል፣ እድምተኛው ‹‹አሜን የሪ ጨኔ›› (አሜን የእግዚአብሔር ፈቃድ ይሙላ) በማለት ይቀበላል፡፡ በመጨረሻም ወንዱም ሴቱም ‹‹አትደንግጪ፤ አታስቢ፤ ልጅሽን አጥብተሽ ለማሳደግ ያብቃሽ፡፡›› በማለት መልካም ተመኝተው ወይም መርቀው ይሰናበታሉ፡፡ ከዚህ ሌላ የሸካቾን ባህል ከኦርቶዶክሳዊነት ጋር የሚያመሳስለው ደግሞ ሕፃኑ አንገት ላይም ጥቁር ክር ወይም ቃንጫ ማሠራቸው ነው፡፡ ይህንንም ቃንጫ ከአንገት ማውለቅ ጉዳት እንዳለው ይታመናል፡፡

## ፫. ሥርዐተ አምልኮ በሸካቾ

በዚኽ ክፍል የሸካቾን ሥርዐተ አምልኮ መመልከት ያስፈለገው ሃይማኖታዊ መመሪያዎችንና የባህላዊ ክንዋኔዎቹ ዐላማ ሃይማኖታዊ ጉዳይ ብቻ መኾኑን ለመግለጽ ነው፡፡ ይኹን እንጂ አስቀድመን የጠቀስናቸው ባህላዊ ክንዋኔዎችም የሥርዐተ አምልኮ አሻራ እንዳረፈባቸው መገንዘቡ አስፈላጊ ነው፡፡

ሕዝቡ ለፈጣሪው የሚገዛበት ወይም አምልኮውን የሚገልጽበት መንገድ በዐይነቱ ሰፊ ነው፡፡ በዚኽ ጽሑፍ የምንመለከታቸውም ከበዐላት እና ክርስቲያናዊ ሕይወት ጋር የተያያዙትን ብቻ ነው፡፡ ከባህላዊ ክንዋኔዎች እንደ ምንረዳው በሸካ አንድ ፈጣሪ ‹‹የሪ›› አለ ተብሎ ይታመናል፡፡

‹‹የሪ›› መልካም በመሥራትና መልካም ዋጋ በመክፈል ‹‹የነተ›› (ገነት) ያስገባል፡፡ በተቃራኒውም መልካም ያልሠሩትን ‹‹ሼሎና ሼፎ›› (ሲኦልና ሰይፍ ያለበት) ይጨምራል፡፡ እንደ ዚኹም ለክፉ ሥራ የበረታና የሚተጋ ‹‹ይኖ›› ተብሎ የሚጠራ ርኵስ መንፈስ አለ ተብሎ ይታመናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከሌሎች ፍጡራን የምትበልጥ፣ የሴቶች መከታ የኾነች፣ ርስበርስ በሚያደርጉት ግንኙነትም በማያዳግም ሁኔታ መሐላ በመፈጸም የሚተማመኑባት «ጨየ ማራሚ» (ጽዮን ማርያም) መሆኗን ለበዐላቱ ከሚደረጉት ክንዋኔዎች መረዳት ይቻላል፡፡ በሸካቾ ብሔረሰብ ከ‹‹የሪ›› (የሁሉ ፈጣሪ) ቀጥሎ ‹‹ጨየ ማራሚ››፣ ከ‹‹ጨየ ማራሚ›› ቀጥሎ «ቡለፎ» (የቃልቻ ዐይነት) በየማዕረጋቸው ይከበራሉ፤ ይፈራሉ፡፡ አውግቸውም ሆነ የአጥኚ ቡድኑ ‹‹የሪ›› (የኹሉ ፈጣሪን) ከላይ አድርጎ የ‹‹የሪ›› ፍጡር የሆነውን ‹‹አዳሞቺ››[26] እና ‹‹ቡለፎ›› የሚመሩት ትልቅ የቃልቻ መዋቅር እንዳለ አቅርበዋል፡፡[27] በተወሰኑ አካባቢዎች (በአንደራቻና በማሻ ወረዳዎች) በጸበልነት የሚጠቀሙባቸውን ቦታዎች ለበረከትና ለፈውስ መጠቀማቸውና በጸበሉ ሥፍራ ለመጠቀም የጥንቃቄያቸው ሥርዐት (የንጽሕና አጠባበቅ፣ የርኵሰት ሕግ ማክበር ወዘተርፈ) የእምነታቸውን መሠረት የሚጠቁሙ ናቸው፡፡ እነዚህን ጉዳዮች እንደ ጥቆማ ተቀብለን ቀጥለን የኦርቶዶክሳዊ ተዋሕዶነት ልዩ ሥርዐት የሚታይባቸውን የበዐላትንና የአጽዋማትን ሥርዐት እንመልከት፡፡

**ጮሞ (ጾም)**፡- በሌሎች ክፍሎችም እንደ ተጠቀሰው የሸካቾ ብሔረሰብእ ዐቢይ ጾምን፣ ረቡዕንና ዐርብን ይጾማል፡፡ ከግራኝ አሕመድ ጋር ከተደረገው ጦርነት በፊት ዐቢይ ጾምን ለ፰ ቀናት ይጾም እንደነበረ ይተረካል፡፡ የጎሣ መሪዎችና በባህል ጉዳይ ላይ ጠንካራ አቋም ያላቸው ሽማግሌዎች (ክርስትና ያልተነሡትም ጭምር) ዛሬም ድረስ ረቡዕንና ዐርብን ይጾማሉ፡፡ ብዙ የጎሣ መሪዎች[28] ረቡዕንና ዐርብን የሚጾሙት በሃይማኖት እንደታዘዙ አምነው ሳይኾን በባህሉ ምክንያት ብቻ ነው፡፡ በጾምና በበዐላት ጊዜያት ደም ማፍሰስ፣ ጋብቻ መፈጸም፣ በባልና ሚስትነት አብሮ መተኛት ክልክል መሆኑን ኹሉም የብሔረሰቡ አባላት የሚያከብሩት ትውፊት ነው፡፡[29]

ዐቢይ ጾምን በተመለከተ የሚነገር አንድ ጠቋሚ ሥነ ቃል መመልከት ይቻላል፡፡ ‹‹ሺቾ ጮሚቃ ሺፓ ኢታታቼ›› (፰ ቀን ጾሜ ፌጦ (የጎመን ዐይነት) አልበላም የሚለው አባባል ዐራት ዐበይት ጉዳዮችን ያስረዳናል፡፡ ይኸውም፡- ፩. ሕዝቡ ጾም ይጾም እንደ ነበረ፣ ፪.ጾሙ ለ፰ ቀናት እንደ ኾነ፣ ፫. በጾሙ የሚመረጥ (የሚበላና የማይበላ) የምግብ ዐይነት በመኖሩ ጾሙ ሰውነትን የሚጎዳ መኾኑን፣ እና ፬. በጾም ፍቺ ከጎመን የተሻለ የተመረጠ ምግብ መኖሩን ያመለክታል፡፡ ስለዚኽም በወቅቱ ለነበረው አኗኗር የጾሙን ቀናት ማሳጠርና (ወደ ሦስት ቀናት ነው) በቀሩት ቀናት የተሻለ የተባለውን መመገብ እንደ ሚገባ መወሰናቸውን ያስረዳናል፡፡

---

[26] አዳሞቺ ከሐሙስ ቀን ጋር እንደ ሚያያዝ ወደ ፊት የምናየው ሲኾን ይኽን አዳሞቺ የሚሉት የፍጥረት መጀመሪያ አዳምን ነው እንድንል የሚያደርጉን ምክንያቶች አሉ፡፡ የመጀመሪያው ቀኑ በየሳምንቱ ለእርሱ መከበሪያነት መዋሉ ከአዳም ሐሙስ ጋር የሚገናኝና በዘመናት ብዛት የተሻሻለ ሊሆን የሚችል፤ ኹለተኛም አዳሞቺ ከኹሉ ቃልቻዎች በላይ ኾኖ በመጀመሪያ ተፈጠረ ከተባለ በእግዚአብሔር የተፈጠረ የአዳም የመጀመሪያው ሰውነቱ ጋር ይገናኛል፡፡ እነዚህን ኹለት መነሻዎች ወስደን ‹‹አዳሞቺ የተባለው አዳም ነው›› ብንል የቀና ሐሳብ ነው፡፡

[27] አውግቸው፣ ገጽ ፶፫-፶፯፡፡ አጥኚ ቡድን ገጽ ፲፰-፲፱፡፡

[38] በሸካቾ ውስጥ ያሉ ኹሉም ዋኖቹ ጎሣዎች መሪ አላቸው፡፡ መሪዎቹ በጣም የተከበሩ ከመሆናቸውም በላይ ሥራ መሥራት አይፈቀድላቸውም፡፡ በተወሰነ ደረጃም ቢኾን ለእነርሱ ማገልገል በረከት (ክህነታዊ ይመስላል) ያስገኛል፤ ለጎሳ መሪዎቹ አለመሥራትም መከራ ያመጣል ተብሎ ይታመናል፡፡ የዕድሜ ገደብ ሳይኖርበት በሕዝብ ምርጫ ከተደረገ በኋላ ከፍተኛ ክብርና ማኅበራዊ ሓላፊነት የሚሰጥባቸው ሲኾን በሕይወታቸው ባህልንና ሃይማኖትን (መጾም፣ መባረክ፣ ወዘተ.) እንዲያጠብቁ መፈለጉ ምናልባት ከነበረው የካህናት ሕይወት ጋር እንዲመሳሰል ተፈልጎ ይሆን? ያሰኛል፡፡ ለምሳሌ በሃይማኖት ሕግ የመስቀል ደመራ በዐል የሚከበረው በቅዱስ ቦታ በቤተ ክርስቲያን ነው፡፡ በሸካቾ ግን የመስቀል ደመራ የሚከበረው በንጉሡ ዘንድ ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያንና ካህን አለመኖሩ ያመጣው ለውጥ እንጂ ቀድሞ ክህነታዊ አሠራር የነበረ ይመስላል፡፡ አውግቸው፣ ገጽ ፵፩-፵፯፡፡

[39]በሸካቾዎች ዘንድ የኹለቱን አጽዋማት መኖር ከተረዳን በቤተ ክርስቲያን የሥርዐት መጻሕፍት የሌሎች አጽዋማት ክብራቸው እንደ ጌታ ጾምና እንደ ረቡዕና ዐርብ ስላልሆነ ጭራሽ ለመረሣት በቅተው ይኾናል፡፡ ሲጾሙ ኑረው የተውበት ዘመንና ምክንያት ሊኖር ይችላል የሚል ግምት መውሰድ ይቻላል፡፡

በዚኽ ውሳኔ መሠረትም ዐቢይ ጾምን እያከበሩ የምግብ ምርጫቸውን ግን ለ፰ ቀን የተሠራውን ሥርዐት ቀንሰው ለሦስት ቀን ያከብሩታል፡፡ የሦስቱ ቀን የጾም ሥርዐት በተለይ ከትንሣኤና ስቅለት በዐላት አከባበር ጋር የተያያዘ ስለሆነ በዚያው ክፍል እንመለከተዋለን፡፡

**ባሬ ባሮ (የበዐላት አከባበር)**[30]፡- በዐላት የሰው ልጅ ከቀናት ለይቶ ከመደበኛ ተግባሩ ታጉሎ የተለየ ሥጋዊና መንፈሳዊ ጥቅም ለማግኘት የሚያከብራቸው ዕለታት ናቸው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ በኦሪት ዘሌዋውያን ፳፫፥ ፩-፫ ‹‹እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲኽ ብሎ ተናገረው፡፡ ለእስራኤል ልጆች እንዲኽ ብለኽ ንገራቸው፡፡ የተቀደሰ ጉባኤ ብላችሁ የምታውጁአቸው በዐላቶቼ፣ የእግዚአብሔር በዐላት፣ እነዚህ ናቸው፡፡ ስድስት ቀን ሥራ ይሠራል፤ በሰባተኛው ቀን ግን የዕረፍት ሰንበት ነው፤ የተቀደሰ ጉባኤ ይኾንበታል፤ ምንም ሥራ አትሠሩም፤ በምትኖሩበት ሁሉ ለእግዚአብሔር ሰንበት ነው፡፡ እነዚኽ የእግዚአብሔር በዐላት፣ በየዘመናቸው የምታውጁአቸው፣ የተቀደሰ ጉባኤ ናቸው፡፡…›› ተብሎ የታወጁ ናቸው፡፡

በሸካቾ ባህል በየሳምንቱ፣ በየወሩ፣ በየዐመቱና በየሰባት ዐመቱ አንዴ የሚከበሩ በዐላት አሉ፡፡ በየሳምንቱ ከሚከበሩት በዐላት መካከል ‹‹ኦጊ ሸንበቶ›› (እሑድ ሰንበት)፣ ‹‹ጊሺ ሸንበቶ›› (ትንሹ ሰንበት/ቅዳሜ)፣ ‹‹ማራሚ ቀኖ›› (ማክሰኞ) የሚሉት ይጠቀሳሉ፡፡ ሌሎች በየሳምንቱ የሚከበሩ  በዐላትም አሉ፡፡ እንደዚሁም በየወሩ ከሚከበሩት በዐላት ዋናው ‹‹ሻሼ ማራሚ›› (በሃያ አንድ) ነው፡፡ በየዐመቱ የሚከበሩ ብዙ በዐላትም አሉ፡፡ ‹‹ተሬ ማራሚ›› በየዐመቱ ጥር ፳፩ ቀን ይከበራል፡፡ ይኽው በዐል በሰባት ዐመት አንዴ ተሬ ቆጬ ተብሎ በሴቶች በደማቅ ሁኔታ ይከበራል፡፡[31] ይኽው የብሔረሰቡ በዐል በየሰባት ዐመቱ በተራራ ላይ በተመረጠና ቋሚ ቦታ ላይ ይከወናል፡፡ በብሔረሰቡ ከሚከበሩት በርካታ በዐላት መካከል ጥቂቶቹን እንደሚከተለው ዘርዝር አድርገን እንመለከታለን፡፡

**ማራሚ ኮዶ (በዐለ ማርያም)** ፡- በማርያም ስም የሚከበሩት በዐላት ሦስት ናቸው፡፡ በማርያም ስም የሚከበሩት ሦስቱ በዐላትም፣ ፩.‹‹ሻሼ ማራሚ›› በየሠላሳ ቀኑ ጽዋ በመጠጣት ፤ ፪. ‹‹ነቴ ማራሚ››፣ በዐመት አንድ ጊዜ ጥር ፳፩ ቀን (በአስተርእዮ ማርያም) እና  ፫. ‹‹ተሬ ማራሚ›› (‹‹ተሬ ቆጬ››ም ይባላል)  በሰባት ዐመት አንድ ጊዜ ጥር ፳፩ ቀን የሚከበሩ በዐላት ናቸው፡፡ እነዚኽ በዐላት በአብዛኛው በሴቶች መሪነትና ዋና ተሳታፊነት የሚከበሩ ሲሆን በተለይ ‹‹ነቴ ማራሚ›› እና  ‹‹ተሬ ማራሚ›› ከፍተኛ ዝግጅት በማድረግ በደማቅ ሁኔታ ይከበራሉ፡፡

**ተሬ ቆጬ (በዐለ አስተርእዮ)**፡-  ይኽ በዐል በዘመነ አስተርእዮ የሚከበር በመሆኑ ‹‹ተሬ›› ማለት አስተርእዮ ነው የሚል ትርጉም እንዲሰጥ ያደርጋል፡፡ ሕዝብ በስፋት የሚሳተፍበት ደማቅ በዐል ነው፡፡ የማርያም በዐል የሚባለው በሴቶች ለአንድ ቀን የሚከበር ሲሆን ይኸኛው ደግሞ በወንዶች ተሳትፎ ጭምር መከበሩ የተለየ ያስመስለዋል፡፡[32]

---

[30] የባሮ ወንዝ የታወቀና ከሸካና ካፋ ደኖች የሚመነጭ ትልቅ ወንዝ ሲሆን ከበዐላት አከባበር ጋር የሚያገናኘው ምክንያት ካለ ተብሎ ቢፈለግም ምናልባት የጥምቀትን በዐል ወደ ወንዝ መውረድ ካልኾነ ሌላ ጠቋሚ አስረጅ አልተገኘም፡፡

[31] በየሰባት ዐመቱ አንዴ ስለሚከበረው በዐል አቆጣጠር መረጃ ማግኘት አልቻለም፡፡ በአውግቸው ጽሑፍ የተጠቀሰውና እስከ ቅርብ ጊዜ በሰባት ዐመት አንዴ ሲከበር ከነበረው የጎሣዎች በዐል በቂና ወጥ የኾነ የዘመን አቆጣጠር እንዳለ መረዳት አያዳግትም (አውግቸው፣ ገጽ ፹፯)፡፡

[32] አውግቸው ተሬ ቆጬን ለይተው ያልጠቀሱ ሲሆን ሽማግሌዎቹ ግን ለብቻው ደማቅ የሕዝብ በዐል እንደኾነ አስረድተዋል፡፡ ወቅቱ ግን አንድ መሆኑ ምናልባት ‹‹በአስተርእዮ ዘመን ከጥምቀት እስከ አስተርእዮ ማርያም በተከታታይ የሚከበርበት ሁኔታ የነበረ ይሆን›› ያሰኛል፡፡ በእርግጠኝነት ለመናገር ግን ተጨማሪ ጥናት ማድርግ ያስፈልጋል፡፡ የጥንት በዐል አከባበር ባልጠፉባቸው እንደ ጎንደር ባሉ ቦታዎች የአስተርእዮ በዐል አከባበር መድመቁን ሥናይ ሀገር ዐቀፍ የኾነ አንድነት የነበረው ይመስላል፡፡

አንድ ምሰሶ ያለው ዳስ ከቆጮ ቅጠልና ከእንጨት ሠርተው የአንድ ቤተሰብእ አባላት በየቍጥራቸው አንድ አንድ ጋን ‹‹ዶጮ›› (ጠላ) ሞልተው በመብልና በመጠጥ የሚያከብሩት በዐል ነው፡፡ በዐሉን ለዐራት ቀን በእልልታ ሲያከብሩ ቆይተው ጋኑን ይዘጉታል፡፡ የዘጉትን ጋን እስከ ዐመት አይከፍቱትም፡፡ ከዋናው ጋን ጠላ ከቤተሰቡ ውጪ ለሌላ ሰው አይሰጥም፡፡ ይህ የሚደረግበት ምክንያትም ጠላው የተለየ ስለሆነና ሰዎች ምናልባት የረከሱ ከሆኑ እንዳይቀምሱት ተብሎ ነው ይባላል፡፡ ‹‹ተሬ ማራሚ›› ወይም ‹‹ተሬ ቆጮ›› ተብሎ በሰባት ዐመት አንዴ የሚዘጋጀው በዐል እጅግ የደመቀና ብዙ የድግስና የጭፈራ ሥርዐት ያለው ነው፡፡ በዚኽ የማርያም በዐል ዑደት ተከትሎ ሴቶች በየወሩ ጽዋ ይጠጣሉ፡፡

**መሽቀሮ**፡- ይኽ የብሔረሰቡ የመስቀልና የዘመን መለወጥ የሚከበርበት በዐል ነው፡፡ ንጉሡ በሚገኝበት አቅራቢያ ባለው ተራራ[33] የሚቃጠለው ደመራ የቀረባቸው ሰዎች ወደ እዚያው በመሄድ፣ የራቃቸው ደግሞ የጎሳው መሪ ዘንድ ተሰብስበው ደመራ የሚያቃጥሉበት ዕለት ነው፡፡፣ በዚህ የበዐል አጋጣሚ የሸካቾ ንጉሥ ዐዋጅ የሚነገርበት፣ የንጉሡ አማካሪዎች (ምክረቾ) ሹመትና ሽረት የሚደረግበት ነው፡፡ በቅርብ ካሉት ጎሳዎች ከእያንዳንዳቸው አንዳንድ ተወካይ፣ ርቀው ከሚኖሩት የብሔረሰቡ አባላት ኹለት ተወካዮች ይመርጣሉ፡፡ የተመረጡትም የንጉሡ አማካሪዎችና የምክር ቤቱ የጉባኤ አባላት ሆነው ያገለግላሉ፡፡[34]

በንጉሡ ዘንድ ኹሉም ሰው አንድ ላይ ተሰብስቦ ድግስ ያዘጋጃል፡፡ መጀመሪያ ንጉሡ ደመራውን (አንዱን ትልቁን ምሰሶ) ካቆመ በኋላ ሌላው ሕዝብ በመጨመር (እንደ ችቦ) ይደመርበታል፡፡ በንጉሡ ቤተሰብ መሪነት ደመራውን አቃጥለው በጭፈራና በመብል መጠጥ በደስታ ያድራሉ፡፡ በጭፈራው ‹‹ኦሆ ሚሽራቻ - እነኾ የምስራች›› በማለት በዐሉን የተመለከተና ሌሎች ወቅታዊ ጉዳዩች በአውራጅና ተቀባይ ሲጨፈር የእግዚአብሔር ሥራም በደግነቱ ይወሳል፡፡ የደመራው ማግስት ‹‹ቱለፋቶ›› (ዐመድ መቀቢያ) ይባላል፡፡ ከደመራው ዐመድ በመውሰድ ግንባር ላይ በመቀባት መድኀኒት ነው ብለው ያምናሉ፡፡ ከንግሥናው ሥርዐት መፍረስ በኋላም ይኽ የደመራ በዐል አልቀረም፤ በታላቅ ሽማግሌ ወይም የጎሣ መሪ የመኖሪያ አካባቢ የደመራ ሥርዐቱ ይፈጸማል፡፡ ንጉሡና አማካሪ ባለስልጣናት የሚወያዩበትና የሚወስኑበት በዐል በመሆኑ ንጉሡ በዚኽ ቀን ሹም ሽር ያደርጋሉ፡፡[35]

**ጋኖ (ገና)**፡- ይኽ በዐል በሌላ አጠራር **ሆሊካሶ** ይባላል፡፡ አጠቃላይ ስያሜውንና ለበዐሉ አከባበር የሚደገሰውንና ጨዋታዎችን እንጂ ለምን እንደ ሚከበር አብራርቶ የሚነግረን አላገኘንም፡፡ ከሚከተለው የበዐሉ መገለጫዎች ግን እንደሌሎቹ የሀገራችን አካባቢዎች ተመሳሳይ የገና በዐል በሃይማኖት ምክንያት ይከበር እንደነበረ ይጠቁማል፡፡ ሆሊካሶ የሚለው ሌላኛው የበዐሉ መጠሪያ ስያሜ በጠማማ እንጨትና ድቡልቡል ኳስ የሚደረግን ጨዋታ ይገልጻል፡፡ ዐዲስ እህል ሲገባ መብልና መጠጥ ተዘጋጅቶ ከጎረቤት ጋር አንድ ላይ ይከበራል፡፡ በዐሉም በወጣቶችና ጎልማሶች የፈረስ ጉግስና ሆሊካሶ (የገና ጨዋታ) በመከወን ይከበራል፡፡

---

[33] የንጉሡ መናገሻ የተመረጠ እጅግ ከፍተኛ ተራራ ቦታ ነው፡፡ አንድራቻ የሚባለው ተራራም የንጉሡ መናገሻ የነበረ ሲኾን በዐፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት በቦታው ስልክ እስከማስገባት የደረሱበትና ዙሪያውን የመከላከያ ገደል (ፈረስ የማይወጣው) የተዘጋጀበት ቦታ ነው፡፡ ደመራው የሚቃጠለውም በዋናነት በዚኹ አካባቢ ነበር፡፡

[34] በንጉሡ ፈቃድ በጥናት ከፍተኛ ሹመት ከሚሰጣቸው ውጪ ያሉት የሕዝቡ ተወካዮች የሚመረጡት በሕዝቡ ነው፡፡ የጾምና መሰል ባህሎችን ማክበር የሚጀምረው ምርጫው ከተከናወነ በኋላ ሊኾን ይችላል፡፡

[35] ይኽ የመስቀል በዐል የዘመን መለወጫ ተደርጎ በሸካ ዞን ባይወሰንም የካፋ፣ የወላይታና የጋሞ ጎፋ ዞኖች አስተዳደሮች የዚኽን በዐል ታሪክና ባህል ዕውቅና ሰጥተው የየዞኖቹ የዘመን መለወጫ ቀን ተደርጓል፡፡ ከዚኽ አንጻር በኢትዮጵያ የደመራ በዐል ብቸኛ ባለቤት የሆነችው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ናት፡፡ በዚኽ ጥናት የተገለጹትን የጠነከሩ ምክንያቶች ባያገኙ ኖሮ አብዛኛዎቹ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተከታይ ያልሆኑ ሰዎች የሚገኙባቸው የወላይታና የጋሞ ጎፋ ዞኖች ነዋሪዎች ይኽን በዐል አያከብሩትም ነበር፡፡ ስለኾነም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በደቡቡ ሀገራችን ክፍል የነበራት መሠረት ይበልጥ አጥንቶ ኀብረ ብሔራዊነቷን በዚኽና በተጨማሪ ጥናቶች መመስከር ይገባል፡፡

**ጋኤወቶ**፡- በመጋቢት ወር የጾም ግማሽ ተብሎ የሚከበር በዐል ነው፡፡ ሥርዐቱን የሚያብራራ ምንጭ አላገኘንም፡፡ የጾም ግማሽ ‹‹በዐል›› ተብሎ ማክበሩን ሥናይ ደብረ ዘይት መሆኑን ከመረዳት ያለፈ ለማብራራት አልቻልንም፡፡

**የሺቂቶሶች ጮኮ**፡- ቀጥታ ትርጒሙ ጌታ ተይዞ የተገደለበት ቀን ማለት ነው፡፡ ዕለቱ ከጾም መፍቻ በፊት ያለው ዐርብ መሆኑና ሕዝቡ ወጥቶ በሽክኛ ዜማ የሚታገዝ ስግደት ማደረጉን ሥናይ ስቅለት ማለት ለመሆኑ ምንም አያጠራጥርም፡፡[36] ዝርዝር ኺደቱን ከትንሣኤ ጋር በተገናኘ ወደ ፊት እናየዋለን፡፡

**ማደ ጉፓ**፡- ስያሜው ገበታ መድፋት የሚል ትርጉም ያለውና የጾም መጀመሪያ ወቅትነቱን መነሻ በማድረግ በየካቲት ወር ውስጥ የሚቀያየር ቢሆንም ዕለቱ ከዚሁ ወር አይወጣም፡፡ የየካቲት ወር የሚጠራውም በዚሁ ስያሜ ነው፡፡ ጾም መያዣን እንደበዐል ማየቱ ግን የቅበላ ሥርዐቱን ደማቅነት የሚያስታውስ ይኾናል፡፡ ይኽ ቀን ግን ከ‹‹ኢየአርግና ኢይወርድ›› ሥርዐት እንዴት እንደሚስማማ ማወቃቸውን ቀጥሎ ካለው የስቅለትና ጾም መፍቻ ዐርብንና እሑድን ካለመልቀቁ ጋር ተያይዞ በከፊልም ቢሆን የአቡሻኽር ዕውቀት ያለውና የሚያሰላ ሰው ከሌለ ቀናቱን እንዴት እንደ ሚጠብቁ ማወቅ አልተቻለም፡፡ ይኽን ቀን ዐረጋውያን ከኾኑት ሰዎች ለይተው ለሕዝቡ የሚያስታውቁ እንዳሉ ሽማግሌዎቹ ይናገራሉ፡፡

**ማደ ካም (ጮመ ቢቾ)**፡- ጥሬ ትርጒሙ ገበታ ማቅናት ሲሆን የጾም ፍቺ ማለት ነው፡፡ ጮመ ቢቾ ማለትም ቀጥታ የጾም ፍቺ ማለት ነው፡፡ እዚህ ላይ የጾሙን አጀማመርና ፍስክ በመጠኑ ዘርዝር አድርገን እንየው፡፡

የሁዳዴን ጾም ‹‹ሺቾ ጨሚቃ ሺፓ ኢታታቼ›› (፳ ቀን እየጾምኩ ፌጦ (የጎመን ዐይነት ነው) አልበላም በማለት ወደ ኹለት ቀን እስኪያሳጥሩ ድረስ በወቅቱ የጾሙ ረጅምነት እስኪከብዳቸውና እስኪሸነፉ ድረስ እየጾሙ መቆየታቸውን ሽማግሌዎቹም ጸሐፊዎቹም ይተርካሉ፡፡[37]ይህ ጾሙን የማሳጠር ውሳኔ ግን መመርመር ይፈልጋል፡፡ ለምሳሌ ጥቅሙንና ሃይማኖታዊ ቀኖናውን የሚከራከር ወገን አልነበረም ወይስ ከነበረ በሐሳብ ተሸንፎል፣ ጾሙን ከአመጋገብ ጋር የተያያዘውን ሥርዐት ብቻ ቀኑን ቀንሶ ሌላውን የጾም ወቅት ሥርዐት ለማክበር እንዴት ተፈለገ፣ ወዘተርፈ የሚሉት ጥያቄዎች ናቸው፡፡ ከጾሙ መግቢያ ጀምሮ ከመብል መጠጥ ውጭ ያለው የደስታ ድግሥ አለመኖር፣ የባልና ሚስት አኗኗር ውስንነት፣ ወዘተርፈ ለስድሳ ቀናት ያኽል ጸንቶ በጸሎተ ሐሙስ ቀን የጉልባን ሥርዐት መከናወን፤ ዐርብ ዕለት ቀኑን ሙሉ በጾም ሲውሉ አንድ ላይ ከአዛውንት ታላቅ በሆነው ዘንድ ተሰብስበው (አቺቦ፣ታዛቢ መኖር ጾሙ እንዲሰምር ያደርገዋል ተብሎ ይታመናል) ሳር ተቆርጦ መሬት ላይ ተጥሎ ከአዛውንቱ አንጋፋው እየሰገደ በዜማ ሲቀድም በተመሳሳይ መልክ ይከተሉታል፡፡ በዚኽ ሥርዐት እመጫቶች፣ ነፍሰ ጡሮችና ሕፃናት እንዲሳተፉ አይፈቀድላቸውም፡፡ በስግደቱ ወቅት ከሚዜሙት መካከል የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፡፡

| | |
|---|---|
| የሮ! የሮ! የራ ቤቴ | አቤት ጌታ ሆይ/ያለኸው |
| ማራ! ማራ!ኢቶስ![38] | ማረን ማረን ክርስቶስ |
| የሻ! የሻ! ኢቶስ! | ተይዞ የሞተው ክርስቶስ |
| ጋዳ! ጋዳ! ኢቶስ! | በክርስቶስ ጥላ ተያይዘን እንድናለን |

[36] የደቡብ ኦሞን ፲፮ ብሔር ብሔረሰቦች ሃይማኖታዊ ጉዳይ በሚያብራራው የሀገረ ስብከቱ ዘጋቢ ፊልም ላይ ‹‹ጌታችን ልጁን ሲልክ ገደሉበት፣ ስለዚህም ጌታ ወደራሱ ወሰደው›› በማለት የተገለጸውን ከብሔረሰቦቹ ዕውቀት ጋር በማነጻጸር ማየት ይቻላል፡፡ በደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ላይ ከደረሰው ከከባዱ የግራኝ ወረራ ጥፋትና ከብሔረሰቦች ግጭት ጋር ተያይዞ የጠፋ ወጥነት ይኖረው እንደኹ እንጂ ተመሳሳይ ታሪኮች ስለ ጌታችን የእግዚአብሔር ተላኪነትና መሞት ይታወቅና ይታመን እንደነበረ መረዳት ይቻላል፡፡

[37] አውግቸው፣ ገጽ ፶፪፡፡

[38] አውግቸው ‹‹ኢቶስ›› ማለታቸው ኢየሱስ ለማለት ፈልገው ነው ብለዋል፡፡ የ ‹‹ቶ›› ድምፅ ‹‹ኢየሱስ›› ከሚለው ውስጥ በዐይነቱ መራቁን፣ በቤተ ክርስቲያን ተደጋግሞ የ‹‹እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ›› ከሚባለው ዜማ ጋር አስተያይተን፣ ‹‹ኢቶስ›› ያሉት ‹‹ክርስቶስ›› ለማለት ነው ብንል ይሻላል፡፡ ‹‹ኢየሱስ›› የሚል የስቅለት ቀን የጎላ ነባር ዜማ አለመኖሩን ስናገናዝብ ይኽንን ግምታችንን ለእውነታው የቀረበ ያደርገዋል፡፡

ይኽንን ዐራት ዐራት ጊዜ ከተቀባበሉ በኋላ ወደየ ቤታቸው ይገባሉ፡፡ ቆሎ በልተውና ቡና ጠጥተው ዶጮ (ጠላ) ካለ ቀምሰው ያድራሉ፡፡ ቅዳሜ ‹‹ዳዶ ማይ ማዮ›› (ያለ ማባያ መብላት) ደረቅ ተመግበው ያድራሉ፡፡ እሑድ ጧት ወተት ታልቦ በጉርጊዮ (ዛፍ ላይ የሚበቅል የሳር ዐይነት ነው) ወተቱን እየነከሩ “ጮመ ቢቾ” (ጾም ተፈታ) በማለት ዐራት ጊዜ አፋቸውን በማስነካት ጾም መፈታቱን ያበሥራሉ፡፡ ሣሩ ግን ሥሩ ለመድኀኒትነት የሚጠቀሙበት ከመሆኑ በቀር ለምን እንደተመረጠ አይታወቅም፡፡ በአንዳንድ አካባቢዎች ይኽ ሥርዐት በመጠኑ የተለየ ቢሆንም ጾምና ፍስክ እንዲሁም ስግደት መኖሩ አንድ ያደርገዋል፡፡ ይህ ሥርዐት እስከ ፲፱፻፺፮ ዐ.ም. ድረስ በየዐመቱ በተወሰኑ የአንድራቻ ወረዳ ሸማግሌዎች ሲፈጸም እንደቆየ ቃለ መጠይቅ የሰጡ ሽማግሌዎችም ተሳታፊ እንደ ነበሩ አስረድተዋል፡፡

**አሙሾ ባሮ**፡- የሐሙስ በዐል ማለት ሲሆን ከትንሣኤ በኋላ የመጀመሪያው ሐሙስ ኾኖ በዐዲስ ዕርድ ጭምር የሚከበር ነው፡፡ ከሐሙስ በተጨማሪ ‹‹ባሮ አቦ›› እና ‹‹ባሮ አቾ›› የዐርባኛ እና የሐምሳኛ ቀን በዐላት መኖራቸው እንጂ ሥርዐታቸው አልተብራራም፡፡ ዐርባኛው ቀን ግን ኹሌ ሐሙስ ላይ ስለ ሚውል ከሌሎች የሐሙስ በዐላት ጋር ተቀላቅሎ ተረስቶ ሊሆን ይችላል፡፡ ሐሙስን ወደ ፊት እንደምናየው ቀኑ ራሱ በቤተ ክርስቶያን ‹‹አዳም ሐሙስ›› መባሉ፣ በኋላም ‹‹እግዚአብሔር በመጀመሪያ የፈጠረው መንፈስ›› ተብሎ ‹‹አዳሞቺ›› የተባለ የቃልቻ በዐል በሐሙስ ቀን መከበሩ፣ በቤተ ክርስቲያን ሌላ ሐሙስ ከአዳም ጋር ተያይዞ እንደዚህ የሚከበር አለመኖሩን ሥናይ የትንሣኤው ማግሥት ሐሙስ ደማቅ አሻራ መተውን እንረዳለን፡፡ ትንሣኤም አሁን በሌሎች አካባቢዎች እንዳለው ሰፋ ብሎ ይከበር እንደነበረና የክርስትናውም ማዕዘን መሆኑ ይታወቅ እንደ ነበረመረዳት ይቻላል፡፡

**ቢሌ ሚካሪ እና ዮሲ ሚካሪ**፡- ቢሊ ሚካሪ የበጋው ሚካኤል (የኅዳር ሚካኤል) ዮሲ ሚካሪ -ክረምቱ ሚካኤል (የሰኔ ሚካኤል) ተብለው በደማቅ ድግስና ጭፈራ የሚከበሩ የወንዶች በዐላት ሲሆኑ በጽዋ የሚዘከሩ ናቸው፡፡ ቅዱስ ሚካኤል በዐመት ውስጥ ያሉትን ሁለቱንም በዐላት ማክበሩን ጨምሮ አቶ አውግቸው የጠቀሱት በዋሻ ውስጥ ካሉት ጽላቶች አንዱ የቅዱሱ መልአክ መሆኑን ሥናይ በዐላቱ መኖራቸው ተቀብረዋል የሚባሉት ጽላቶች ሊኖሩ እንደሚችሉ ተጨማሪ ጥቆማ ይኾናሉ፡፡

**አውራቲ**፡- ትርጒሙን በቀጥታ ለመተርጐም አውራቲ ኅርፍ ከሚለው ቃል ጋር የሚያይዙ ሽማግሌዎች አጋጥመውናል፡፡ ይኹን እንጂ ከዚኽ ቀን በኋላ ለኹለት ተከታታይ ሳምንታ ወንዶች ብቻ ማክበራቸው ከኅርፍ ጋር የተያያዘ የሚከበር ታሪክ ባለመኖሩ ይልቁንም የቤተ ክርስቲያን ብዙ ትምህርቶች በመዘንጋታቸው እንጂ አውራቶ (የሐዋርያት በዐል) ነው ማለት ይቻላል፡፡[41]

የኅዳርና የሰኔ ሚካኤልን የሚያከብሩት ወንዶች ከአውራቶ ጀምሮ በየሳምንቱ ሁለት ጊዜ ጽዋ እየጠጡ በመዘከር ነው፡፡ በችግራቸው ጊዜ ‹‹የእነዚህን መላእክት ስም›› በመጥራት በክንፍ ይጋርዱናል ብለው ያምናሉ፡፡ ምግብ ለመባረክ ‹‹ማራኮ ሺቻላ - መላእክት ይቅደሙ›› የሚባልላቸው ከቅዱስ ሚካኤል በተጨማሪ ሌሎች መላእክት እንደሚታወቁ ያስረዳል፡፡

ከአውራቶ ቀን በሳምንቱ ያለውን ሲያከብሩ የቅዱስ ሚካኤልን ክብረ በዐል ከላይ በገለጥነው መሠረት ማክበራቸው ስለሚታወቅ ቅዱስ ሚካኤልን ነው ለማለት አያስቸግርም፡፡ ከአውራቶ በዐል ኹለተኛ ሳምንት ያለው የቅዱስ ገብርኤል በዐል ዐመታዊ መኾኑ ደግሞ በሸካቾ ባህልና ቋንቋ ውስጥ ብዙም የማይታወቀው ቅዱስ ገብርኤል ይከበር ነበር? ጽላትስ ይኖረው ይኾን? ያሰኛል፡፡

---

[39] አውግቸው ግን ከሐዋርያት በዐል ጋር ብቻ ነው ያያዙት (አውግቸው፣ ገጽ ፰-፰፩) ፡፡

እስከ አሁን የተመለከትናቸው የበዐላት አከባበሮች ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ በሸካቾ በዐላቱ የሚከበሩት በቂ ዝግጅትና ትኩረት በማድረግ ነው፡፡ ሰንበትንም የሚያከብሩት ከቅዳሜ ጀምሮ ነው፡፡ ስለ በዐላቱ አከባበር የተመለከትነውን በሚቀጥለው ክፍል ስለ ቀናትና ወራት አቆጣጠር ከቀረበው ዝርዝር ጋር አገናዝበን ሥናይ በሸካቾ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት በጥልቀት ይታወቅ እንደነበር እንገነዘባለን፡፡ በብሔረሰቡ ዘንድ ሥር ሰዶ የነበረው የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ክርስትና እምነት በካህን እጦት፣ በትምህርት እጥረትና በጊዜ ብዛት የተዘነጋ ወይም የተቀላቀለ ይመስላል፡፡ ይኽን በሚመለከት አጥኚ ቡድኑም ገጽ ፲፰ ላይ ነሐሴ ፴ ቀን ፲፱፵፪ ዐ.ም. የተጻፈን የአስተዳደር ዘገባ ጠቅሶ ‹‹በግራኝ ወረራ ምክንያት ቀደም ሲል ገኖ የነበረው የክርስትና እምነት ተዳከመ፤ በዚህም ምክንያት አብዛኛው ሸካቾ የባዕድ አምልኮ ተከታይ ሆነ›› ይላል፡፡ ይኽም ኾኖ ይኽ ቀረው የማይባል ጠንካራ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ክርስትና እምነት በብሔረሰቡ አባላት ዘንድ እንደ ነበር መረዳት ይቻላል፡፡[40]

## ፩. የሸካቾ የቀን አቆጣጠር

የሸካቾ የቀን አቆጣጠር እንዲኹም የዕለታትና የወራት ስያሜዎች በአብዛኛው ከኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ክርስትና እምነት ጋር ይዛመዳሉ፡፡ የስያሜ ምንነት ከጊዜውና ከቦታው ነዋሪዎች ቋንቋ እምነትና ባህል ጋር እንደሚያያዝ ግልጽ ነው፡፡[41] የሸካቾን የቀን አቆጣጠር ስያሜያቸውንና ቀጥተኛ ትርጒማቸውን ከዚህ አንጻር ቀጥሎ በቀረቡት ሠንጠረዥ ከአጭር ማብራሪያ ጋር ብቻ ሲመለከቱ ‹‹ቀናቱን እንዲኽ የሠየመው ክርስቲያን ሳይኾን ነውን?›› ብለው ይጠይቁ፡፡ ይኽ ስያሜ የቀናት ብቻ ሲኾን የሰዎች፣ የቦታ፣ የተፈጥሯዊ ሀብቶች፣ የባህላዊና ትውፊታዊ ክንዋኔዎች ስያሜዎችም በቂ ምክንያት እንደ ሚኖራቸው የሚጠበቅና በዘመን ብዛት ትርጒማቸው የማይታወቅ ብዙ አሉ፡፡ የሚከተለውን ሠንጠረዥም ከዚኽ አንጻር ማየቱ ጠቃሚ ስለኾነ ለአንባቢው ቀርቧል፡፡[42]

---

[40] ሽማግሌዎች በግራኝ ዘመን የተነገረ ‹‹በዐሥረኛ ትውልድ የሸካ ታሪክ በስፋት ይነገራል፣ የተቀበሩት ጽላቶችም ይወጣሉ›› ተብሎ አስቀድሞ ትንቢት እንዳለ ይናገራሉ፡፡

[41] ተክለ ጻድቅ መኩሪያ የኦሮሞ ብሔር በቤተ መንግሥት ውስጥ የሥልጣን ድርሻ እንደ ነበረው ያገናዘቡት በሥነ ቃል ውስጥ ያለውን የራስ ደገልሃን አጋፋሪ ቱሉ የተባለውን ሰው ስም ነው፡፡ ‹‹አገባባቸውም (የኦሮሞ) ግራኝ ዐፄ ልብነ ድንግልን ከነሠራዊታቸው አባሮ ሸዋንና የዐማራን ሀገር ሲይዝ እነርሱ ከኋላ እየተከተሉ ሀገሩን ወረሩ እየተባለ በአንዳንድ ታሪከ ነገሥትና በቃል የሚተረከው ከእውነት የዘለለ ሳይኾን አይቀርም፡፡ ኦሮሞች በቃል በዐፄ ልብነ ድንግል ዘመን ከመጡና ከዚያ በፊት ካልነበሩ ዐፄ ልብነ ድንግል 'ሁሉ ቢፈራ ቱሉ እንዴት ፈራ' ብለው የተደነቁበት ከመኳንንቶቻቸው አንዱ አጋፋሪ ቱሉ ከወዴት መጣ፣ ቱሉ ያማራ ስም ሊሆን ነውን;...››(የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ልብነ ድንግል እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ፣ ፫ኛ እትም፣ ገጽ ፺፬)፡፡

[42] በዚኽ አጋጣሚ ተጨማሪ ጥናት የሚፈልጉ ነገር ግን በቂ ጥቆማ የሚሰጡ ተያያዥ ጉዳዮችን ልጥቀስ:: የወላይታ፣ የጋሞና የካፋ ብሔሮች የቀን አቆጣጠር ውስጥ የዘመን መለወጫው የመስቀል በዐል ኾኖ በመንግሥት ደረጃ ዕውቅና ማግኘቱ ይኽም ወላይታና ጋሞ የኦርቶዶክሳዊነቱን ታሪክ እንዲነገር የማይፈልጉ ብዙዎች ባሉበት ወቅት መሆኑ፣ የፕሮቴስታንት እምነት በብዛት ተከታይ ያለበት የሲዳማ ብሔር ውስጥ ስለ ሰንበት ቀንና ቀስተ ዳመናን ‹‹መገኒሴሞ-የእግዚአብሔር ድንግል›› ማለቱ የእግዚአብሔር ድንግል ልትባል የምትችል ብቸኛዋን ድንግል ማርያምን ከቀስተ ዳመና ጋር በምሳሌ የምታመሰግናት ከኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ውጪ ማን አለና ጥንተ ኦርቶዶክስ ሊያሰኘው ስለ መቻሉ፣ እንዲኹም በሙሉ በሚባል ደረጃ ሙስሊም የኾነው የሥልጤ ብሔር ቅዳሜንና እሑድን ‹‹ግድር ሰንበት›› እና ‹‹አን ሰንበት›› ማለቱ በዞኑ አስተዳደር በታተመው የቀን መቁጠሪያ ላይ ጭምር ዕውቅና ተሰጥቶት መውጣቱ፣ ኦርቶዶክሳዊ አሻራውን ሊያስጥለው የቻለው እስልምና በቀን ስያሜ እንኳ ከኦርቶዶክሳዊው መሠረት የተካከለ ታሪክ እንደሌለው ምልክት ሊሆን መቻሉ፣ከእነዚኽ ጋር በተያያዘም በብሔሮች የታሪክ ዝምድና የሚጠቀሱት ከሸካ ጋር የሚዛመዱት የሸናሻና አንፊሎ፣ ከሲዳማ ጋር የሚዛመዱት የቀቤና፣ ሐላባና ዳውሮ፤ ከሥልጤ ጋር የሚዛመደው የሐረሪ ሕዝብ ጉዳዮች ቢጠኑ በወገንተኛ ጸሐፍት ዘንድ የሚባለው ብሔሮቹን ከኦርቶዶክሳዊነት የራቀና ለፕሮቴስታንታዊነትና ለእስልምና የቀረቡ ተደርጎ የሚተረከውን ሊያርም ይችላል፡፡

**የቀናት ስያሜ** [43]

| የሸክኛ ስያሜ | ትርጉም በዐማርኛ | መግለጫ |
|---|---|---|
| ወኒሸኖ | ሰኞ | ስያሜውን ከአገኘበት ሁኔታና ተግባር አንጻር ደግ ቀን ይባላል። ደግ የተባለውም ከቅዳሜ ጀምሮ ዕረፍት ሲደረግ ቆይቶ ሥራ ስለ ሚሠራብት ነው። በዚኽ ቀን የሚሠራው ሥራም በረከትና ረድኤት አለው ተብሎ ስለሚታመን ነው። በሸክኛ ቋንቋ ‹ወኒ› ማለት መጀመሪያ ማለት ነው። |
| ማግሸኖ | ማክሰኞ | ማግሸኖ ‹‹ማራሚ ቄሞ›› (የማርያም ቀን) ይባላል፤ ‹‹በዚህ ቀን ማርያም ብትለመን ትሰማለች›› ይላሉ። ሳይሠሩ በጾምና በጸሎት የሚውሉ አሉ፤ በዕለቱ በተለይ እናቶች ‹‹ማርያም በዚኽ ቀን ተወልዳለች ቃል ኪዳንም እሰማለሁ ብላለች›› ይላሉ። በኅዳር ወር የመጀመሪያው ማክሰኞ ‹‹ጨዩ ማራሚ›› (ጽዮን ማርያም) ከእስራኤል የመጣችበት እንደ ኾነ ይታመናል። ማክሰኞን የቻለ በስሟ ጠላ በጥብጦ ዳቦ ወይም ቂጣ ቆርሶ ቡና አፍልቶ ማክበር የአብዛኛው አዛውንት ሴቶች ልማድ ነው።[44] ከአሮጊቶች በስተቀር ለሌሎች የሥራና የበረከት ቀን ነው ተብሎ ይታመናል። |
| ኦሮቦ | ረቡዕ | ‹‹ሸማታቴኖ አቦ›› (የሰማይ ንጉሥ ቀን) ሲኾን በጾም በጸሎት ይዋላል። ይኽ ዕለት ‹‹ገፊ›› ነው ስለሚባል ብዙ አይወደድም። ንብ አትገባም ተብሎ ስለሚታመን በረቡዕ ቀን ቀፎ አይሰቀልም። ትርፍ አይገኝበትም ስለሚባልም ለንግድ አይወጣም። አይበቅልም፤ ቢበቅልም ፍሬው እምብዛም ነው ተብሎ በመታመኑ ዘር አይዘራም። በአጠቃላይ ‹‹ረድኤትና በረከት የሌለው ቀን ነው›› ብለው ያምናሉ።[45] |
| አሙሾ | ሐሙስ | ‹‹አሙሾ አዳሞ›› (ሐሙስ አዳም) ሲባል አዳሞቹ የተባለው መንፈስ የሚመለክበት ቀን ነው። አዳሞቹ ከጨየ ማራሚ ቀጥሎ የሚከበር መንፈስ ነው። መንፈሱ የተፈጠረው በዚኽ ቀን ነው ተብሎ ይታመናል። ስለዚህ የቃልቻ ቀን ይባላል። አጀማመሩ ለቃልቾች የጉልበት ሥራ ለመሥሪያነት ሲኾን እያደር ግን ማምለኪያ ኾነ። በቃልቻ ለሚያምኑ የበረከትና የረድኤት ልዩ ቀን ነው ተብሎ በመታመኑ ሥራ ይሠራበታል። |
| ሚች ዶኦ | ዐርብ | ትርጉሙ ከማረፍ በፊት የሥራ ማጠናቀቂያ እንደ ማለት ነው። ዕለቱ ቅዳሜና እሑድ ለማረፍ ሥራ የሚጠናቀቅበት በመኾኑ የሥራ ቀን ነው። |
| ግሽ ሻንበቶ | ቅዳሜ | ትንሹ ሰንበት ይባላል። እግዚአብሔር ዕረፍት የጀመረበት ቀን ነው። ያልተጠናቀቀ ሥራ ይጠናቀቅበታል፤ እግዚአብሔር ሙሉ ያረፈበት ሳይኾን የጀመረበት ነውና። |
| ኦጊ ሻንበቶ | እሑድ | ‹‹የሪ ካሻቲ ቄሞ›› (እግዚአብሔር ያረፈበት ቀን) ይባላል። ሙሉ ዕረፍት ተደርጎበታል ተብሎ ይታመናል። ትልቁ ሰንበት የሚል ስያሜ ያገኘው በዚኽም ምክንያት ነው። |

43 የቀናቱ ትርጉም ከጥቂት ማብራሪያ በቀር ከአውግቸው ጹሑፍ የተወሰደ ነው። ይኽ የተደረገበት ምክንያት በቃለ መጠይቅ ከሽማግሌዎቹ ያገኘነው መረጃም ተመሳሳይ በመኾኑ ነው።

44 የመስቀል ደመራን የዘመን መለወጫነት እንደ መነሻ ብናደርግ የኅዳር ወር መግቢያ ማለት ከኅዳር ፲፯ በኋላ የመጀመሪያው ማክሰኞ ለኅዳር ፳፩ የቀረበ መሆኑን፣ ‹‹ጨየ ማራሚ›› የጽዮን ማርያም በዐል መሆኑን እንረዳለን። ይኽ ደግሞ የኅዳር ሚካኤልን የበጋው ሚካኤል ብለው ከማክበራቸው ጋር መታረቅ አለበት። ይኽ ኹሉ ግን በሕዝቡ ግንዛቤ መጠን ዛሬ ባሉት ሽማግሌዎች የሚጠቀስ ስለኾነ የስሌቱ ትክክለኛነት ቦታ ላይሰጠው ይችላል።

45 ቀኑን ‹‹የሰማይ ንጉሥ ቀን›› ካሉ በኋላ ‘ገፊ’ ማለታቸው በዚኽ ቀን ጌታችንን አይሁድ ሊገድሉት እንደተወሰነበት ይታወቅ የነበረውን የሚጠቁም ይመስላል።

## የወራት ስያሜ

| የሽክኛ ስያሜ | የዐማርኛ ትርጕማቸው | መግለጫ (ስያሜውን ከአገኙበት ኹኔታና ተግባር አንጻር) |
|---|---|---|
| መሽቀሬ | መስከረም | ‹‹የመስቀል ወር›› ማለት ሲኾን መስከረም ወር ውስጥ በሚከበረው የመስቀል በዐል ‹‹መሽቀሮ›› የተሠየመ ነው፡፡ |
| መጥጆ | ጥቅምት | ብራ (መከር) ማለት ነው፡፡ ‹‹ጨጠ ቢዩ›› (የንጉሥ ማር) የተባለው የሚቆረጥበት ወር ነው፡፡ በተጨማሪም የጨበር (ማዎ) ኀሣ ቅዱስ ሚካኤልን የሚያከብርበት ዕለት ነው፡፡ |
| ቢሊ ሚካሪ | ኅዳር | ‹‹የበጋው ሚካኤል ወር›› ማለት ሲሆን በኅዳር ወር ውስጥ በሚከበረው የ‹‹በጋው ሚካኤል›› በዐል ምክንያት የተሠየመ ነው፡፡ |
| ጋኖ/ሆሊ ካሶ | ታኅሣሥ | ‹‹ሆሊ ካሶ›› ገና ጨዋታ እንደማለት ነው፡፡ በታኅሣሥ ወር በሚከበረው የክርስቶስ ልደት ተሰየመ፡፡ ‹‹ሆሊ›› መጫዎቻ ሩር ማለት ሲሆን ‹‹ካሶ›› ደግሞ ቆልማማ መምቻ ማለት ነው፡፡ |
| ተሬ ማራሚ | ጥር | ‹‹የአስተርእዮ ማርያም ወር›› ማለት ነው፡፡ ጥር ውስጥ በሚከበረው አስተርእዮ ማርያም በዐል የተሠየመ ነው፡፡ |
| ደጌ አጋኖ | የካቲት | መካከለኛው ወር ማለት ነው፡፡ መደጉፖ ነው የሚባለው ያሉን ሽማግሌዎችም አሉ፡፡ |
| ማደጉፓ | መጋቢት | መሶብ (ገብቴ) ተደፋ፤ ቅበላ ተደረገ ማለት ነው፡፡ የጾም መግቢያ ወርነቱ የተገለጸበት ነው፡፡ ‹‹ጋኤወቶ›› ነው የሚባለው ያሉን አሉ፤ በትርጕም የጾሙ እኩሌታ የሚውልበት ወር ለማለት ነው፡፡ |
| መደካሞ | ሚያዚያ | መሶብ/ገበቴ ቀና፣ ፍስክ ኾነ ማለት ነው፡፡ ይኽም የጾም ማብቂያውን በሚገልጽ መንገድ የተሠየመ ነው፡፡ |
| ባራአቦ | ግንቦት | የዐርባኛው በዐል ወር ማለት ነው፡፡ የክርስቶስ ዕርገት በግንቦት ይውላልና፡፡ |
| ዮሲ ሚካሪ | ሰኔ | ሰኔ ውስጥ በሚከበረው የሚካኤል በዐል ተሠየመ፤ የክረምቱ ሚካኤል ማለት ነው፡፡ |
| አውራቶ | ሐምሌ | የሐዋርያት በዐል ማለት ሲሆን ሐምሌ ፳ የሚፈታውን የሐዋርያት ጾምና የቅዱስ ጴጥሮስና ጳውሎስ በዐልን በሚገልጽ መንገድ የተሠየመ ነው፡፡ አውራቲ ማለት ጎርፍ ስለሆነ ትርጕሙን ከዚኹ ጋር የሚያይዙም አሉ፡፡[46] |
| ጉዲ (ቁኒ) | ነሐሴ | አስፈሪ/ጭጋግ የበዛበት ማለት ሲሆን ክረምትነቱን በሚገልጽ መንገድ የተሠየመ ነው፡፡ እንዲኹም የዘር ማለቂያ (የረሀብ) ወር ይባላል፡፡ ዘር ከቤት ተሟጦ ማሳ ላይ ስለሚዘራ፡፡ |
| ጳቂ | ጳጉሜ | ነጠላ ትንሽ ማለት ነው መጠንን ለመግለጽ፡፡[47] |

[46] ጎርፍ የሚበዛበት ወር ለማለት ግን ከውነው ብዛት አንጻር ከሐምሌ ይልቅ ነሐሴ ይሻል ነበረ፡፡ የሐዋርያት በዐልን መመልከቱ የበለጠ አሳማኝ ይመስላል፡፡

[47] በማንኛውም አቆጣጠር የጳጉሜን ወር ፲፫ኛ አድርጎ የሚቆጥር ከኦርቶዶክሳውያኑ አብያተ ክርስቲያናት በቀር ሌላ የለም፡፡ ወር ተብላ ግን አጭር መሆኑዋን በስም የገለጡት ከፀሐይ ዑደት ጋር የምትቆጥር ቤተ ክርስቲያንን ባያውቁ ከየት ያመጡታል

## ፰. ማጠቃለያና አስተያየት

የሸካቾን ብሔረሰብእ ባህልና ቋንቋ በስፋት ማጥናት ቢቻል ማስረጃ ለሚፈልገው ዘመናዊ ትውልድ ቤተ ክርስቲያንን የጥቂት ብሔሮች አድርገው ለሚናገሩና ለሚጽፉ ይኽን ንድፈ ሐሳብ ማፍረስ እንደሚቻል መገመት የጥናቱ መነሻ ምክንያት ነው፡፡ በዚኽ ጥናት የዳሠሥናቸውንና ከአፈ ታሪኩም ኾነ ከጸሐፍቱ ያገኘናቸውን ሐቆች ብንደምራቸው ሸካቾ ሙሉ ኦርቶዶክሳዊ እንደነበረ ለማረጋገጥ የሚያስፈልገው ቀላል አመክንዮ ነው፡፡

አንድን ባህል ወይም ቋንቋ በብሔር ደረጃ ወጥነት ያላቸው ሐሳቦችን ለማንጸባረቅ የሚፈጀውን ጊዜ ከነገሥታቱ ዘመን ሥልጣኔ አንጻር ስናገናዝበው ዐመታትን እንደ ሚወስድ የትውልድንም ቅብብል እንደሚፈልግ ግልጽ ነው፡፡ ከዚኽ አንጻር በዚኽ ጥናት ያየናቸውን ኦርቶዶክሳዊ ምንጭ ያላቸውን አሻራዎችና የደበዘዙትን ዶግማዊና ቀኖናዊ ትውፊቶች ስንመለከት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሸካቾ ሕዝብ ውስጥ መሠረት እንደ ነበራትና ከበድ ያሉ ፈተናዎች እንዳጋጠሟት መረዳት ይቻላል፡፡ በዚኽ ዘመን የቴክኖሎጂው መስፋፋት ፈጣን መኾንና ለባህሉና ለቋንቋው ቅርብ የኾኑ ሰዎች እያረጁና በሞት እየተለዩ መኼዳቸው በዚኽ ጥናት ያልተመለሱትን ለመመለስ ተጨማሪ ጥናቶችን በአስቸኳይ ማካኼድ ይገባል፡፡

የቅርብ ዘመን ነገሥታትን (ዳግማዊ ምኒልክንና ከዚያ ወዲኽ ያለውን) ታሪክ አላግባብ መጥቀስ ተገቢ አለመኾኑን ከዚኽና መሰል የጥናት ውጤቶች መረዳት ይቻላል፡፡ ከጥናቱ መገንዘብ እንደሚቻለው ቤተ ክርስቲያንን ከባለቤትነትም ኾነ ከ‹‹ያገባኛል›› ባይነ ለማራቅ የሚጠቀስባት ‹‹የተለያዩ ብሔሮችን፣ ብሔረሰቦችንና ሕዝቦችን ለይቶ በዳይነት›› ምክንያታዊነትና አሳማኝነት ያለው አይደለም፡፡ ለሃይማኖትም ኾነ ለሀገር ጥቅም የሚያስፈልጉ እውነታዎችን በጥልቀት ማጥናትና ለአደባባይ ማብቃት ቤተ ክርስቲያኒቱ በአብዛኛዎቹ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ውስጥ አሻራ ሊኖራት እንደ ሚችል ከዚኽ ጥናት መረዳት ይቻላል፡፡ የሚችሉ ኹሉ ተመሳሳይ ጥናት ለማካኼድ ሊተጉበት የሚገባ ወቅታዊና ታሪካዊ ሓላፊነት መኾኑን ይኽ ጥናት ይጠቁማል፡፡

አስተዳራዊና ታሪካዊ ሓላፊነት ያለባቸው የቤተ ክርስቲያኒቱ ልጆች በዚኽ ጉዳይ ላይ ለመሥራት በአንዳንድ የሀገራችን አካባቢዎች የተፈጠረባትን ግልጽ መገለል ማወቅ ብቻ በቂ ምክንያት ሊኾናቸው ይገባል፡፡ ከየብሔረሰቦቹ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ቤተ ክርስቲያኒቱ የማይመለከታትና ድርሻ የሌላት አድርገው የሚካኼዱ ፖለቲካዊና ጥበባዊ (አንዳንዴም ሣይንሳዊ የሚባሉ) ሥራዎች ማንንም የተሳሳተ አቅጣጫ እንዳያሲዙ ወይም ለቋሚ ስሕተት እንዳይዳርጉ የዚኽን ጥናት ውጤቶችና መሰል ሥራዎች ሊያገናዝቡ ይገባል፡፡
ከግቤ ወንዝ ማዶ የነበረችውን ቤተ ክርስቲያን በስፋት ማጥናት፣ በአፈ ታሪክ የሚነገሩትን እውነታዎችና የተቀበሩ ቅርሶችን መፈለግ ተገቢና ወቅታዊ ነው፡፡ የስያሜዎችን ዋጋ በዚኽ ጥናት እንደአየነው ኹሉ የሲዳማ፣ የወላይታ፣ የጋሞ፣ የሥልጤ እንዲኹም ከእነዚኽ ጋር ተዛምዶ ያላቸውን የሐላባ፣ የቀቤና፣ የዳውሮና የሐረሪ ብሔሮችን፣ብሔረሰቦችንና ሕዝቦችን ታሪክ በተመሳሳይ መልክ ማገናዘቡና መመርመሩ ለቤተ ክርስቲያን ሰፊ ጥቅም ይኖረዋል፡፡